የ30ኛ ዓመት ቁጥር 197 አሶሳ ሐምሌ 18/ 2015 ዓ.ም

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ልሣነ ህግ ጋዜጣ**

የፖ.ሳ.ቁ፣293

ያንዱ ዋጋ------

# LISAN HIG GAZETA

**Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State**

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ አዋጅ**

## አዋጅ ቁጥር 197/2015 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር197/2015 ዓ.ም

የክልሉን የመንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 190/2015 ዓ.ም ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በክልሉ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ ውስን የሆነውን የሕዝብና የመንግስት ሀብት ቁጥብ በሆነ አኳኃን ለመጠቀም በሚያስችል የተቀናጀ አስተዳደርና አገልግሎት በመስጠት ለዘላቂ ልማት እና መልካም አስተዳደር መስፈን ብሎም ድህነትን ለመቀነስ የላቀ ድርሻ እንዳለው በመገንዘብ፤

በአደረጃጀት፣ በአሠራር እና በሰዉ ኃይል የታዩ ችግሮችን ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉን የአስፈጻሚ አካላት አሠራርና አደረጃጀትን በጥናት መፈተሽና የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተበታተኑ ተግባራትን በማሰባሰብና በማቀናጀት የተሻለ ዉጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል፣ ከፌዴራል መንግስት እና ከክልሎች ለሪፖርቲንግና ለስራ ግንኙነት ተቀራራቢ አደረጃጀት መፈጠር እንዳለበት በመታመኑ፤

በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ ቁጥር 3.1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር** 197/2015 **ዓ.ም**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### አንቀጽ 2

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "**የክልሉ ምክር ቤት**" ማለት በተሻሻለዉ የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቋቋመዉ አካል ማለት ነው፤
2. "**ሕገ-መንግስት**" ማለት በተሻሻለዉ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት ማለት ነው፤
3. "**የመስተዳድር ምክር ቤት**" ማለት የክልሉ የህግ አስፈጻሚ አካል የሆነው የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ማለት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ የተዋረድ አስፈጻሚ አካላት ሊጨምር ይችላል፤
4. "**ቢሮ**" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ከፍተኛ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እና እንደ ነገሩ ሁኔታ ሌሎች መሥሪያ ቤቶችን በበላይነት የሚመራ ማለት ነው፤
5. "**ሌሎች መሥሪያ ቤቶች**" ማለት በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጐች መሠረት የተቋቋሙ ወይም የሚቋቋሙ ቢሮዎች፣ ጽህፈት ቤቶች፣ ኮሚሽኖች፣ ባለሥልጣኖች፣ ኤጀንሲዎች፣ ተቋማትንና ሌሎች መሰል አስፈጻሚ አካላትን ማለት ነዉ።

## ክፍል ሁለት

## ስለ አስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች

### አንቀጽ 3

### መቋቋም

1. የመንግስት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና ሕጐችን በሥራ ላይ የሚያውሉና አስተዳደራዊ ተግባሮችን የሚያከናውኑ አስፈጻሚ አካላት እንደሚከተለው ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-
   (ሀ) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት፤
   (ለ) የአስፈጻሚ አካላት የሆኑ ቢሮዎች፤
   (ሐ) ሌሎች ቢሮዎችና መስሪያ ቤቶች እና
   (መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 በተመለከተዉ ድንጋጌ መሰረት የተዋረደ የዞን/የከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ወይም መምሪያዎች ወይም የወረዳ ጽህፈት ቤቶችን ይጨምራል፡፡
2. የሚከተሉት መስሪያ ቤቶች የመስተዳደር ምክር ቤት አባል እና አስፈፃሚ አካላት ሁነው በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

(ሀ) ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፤
(ለ) ግብርና ቢሮ፤
(ሐ) የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ
(መ) መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ፣
(ሠ) የከተማ እና መሰረተ ልማት ቢሮ
(ረ) ሠላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ፤
(ሰ) ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ
(ሸ) ፋይናንስ ቢሮ፤
(ቀ) ፕላንና ልማት ቢሮ፤
(በ) ውሃ እና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ፤
(ተ) ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ፤
(ቸ) ትምህርት ቢሮ፤
(ኀ) ጤና ጥበቃ ቢሮ፤

(ነ) ስራና ክህሎት ቢሮ፤

(ኘ) ሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤

(አ) የመሬትና ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ቢሮ

(ከ) ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ

(ኸ) መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ

(ወ) ገቢዎች ባለስልጣን፤

(ዐ) ፍትህ ቢሮ፤

3. ርዕሰ-መስተዳድሩ የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት እንዲሆኑ በተለይ የሚመረጡ የሌሎች ቢሮዎች ኃላፊዎችና መስሪያቤቶችን ይጨምራል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተዘረዘሩት የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ተጠሪነት ለክልሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤትና ለርዕሰ-መስተዳድሩ ይሆናል።

## አንቀጽ 4

## ስለሌሎች የአስፈጻሚ አካላት መስሪያ ቤቶች

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተዘረዘሩት የአስፈፃሚ አካላት እንደተጠበቀ ሆኖ መስተዳድር ምክር ቤቱ ሌሎች አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፤
2. በዚህ አዋጅ ውስጥ ያልተመለከቱ ሌሎች የክልሉ መንግሥት አስፈጻሚ አካላት በማቋቋሚያ ሕጎቻቸው መሰረት ሥራቸውን ይቀጥላሉ፤
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥራ ላይ ያሉና ወደፊት የሚቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትን በሚመለከት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ መስተዳድር ምክር ቤት፣ ርዕሰ-መስተዳድሩ እና ምክትል ርዕሰ-መስተዳድሩ

## አንቀጽ 5

## መስተዳድር ምክር ቤት

1. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

(ሀ) ርዕሰ-መስተዳድር፤

(ለ) ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር፤

(ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከቱ አስፈጻሚ አካላት የሆኑ ቢሮ/ባለሥልጣን ኃላፊዎች እና

(መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር ከተመለከቱት ውጭ ርዕሰ-መስተዳድሩ የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት እንዲሆኑ በተለይ የሚመርጣቸው የሌሎች ቢሮዎች ኃላፊዎችና ባለሥልጣናት፡፡

2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተመለከተው ማንኛውም አስፈጻሚ አካል በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስብሳባ ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ ምክትሎች ካሉት በግልጽ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ኃላፊ ወይም ሌላ ህጋዊ ተወካይ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምትክ አባልነት ይሳተፋል፡፡

## አንቀጽ 6

## የክልል መስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1 የክልል መስተዳድር ሥልጣንና ተግባሩ የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 59 እና በሌሎች ሕጎች የተመለከቱት ይሆናል፡፡

2 በንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሁኖ የርዕሰ መስተዳድሩን አማካሪዎች ስልጣንና ተግባር ይዎስናል በደንብም እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 7

## የክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ-መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 61 እና በሌሎች ሕጎች ተለይተው የተመለከቱት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 8

## የክልሉ ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር ሥልጣንና ተግባር በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 62 እና በሌሎች ሕጎች ተለይተው የተመለከቱት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 9

## የመስተዳድር ምክር ቤት አሰራር

1. የመስተዳድር ምክር ቤት ፡-

(ሀ) የራሱ የውስጥ ደንብ ይኖረዋል፤

(ለ) በውስጥ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል፤

(ሐ) ምልአተ-ጉባኤ የሚሟላው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፤

(መ) የሚያስተላልፈው ውሳኔ በተባበረ ድምጽ ይሆናል፤ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልተቻለ በድምጽ ብልጫ ይወሰናል፡፡

2. ርዕሰ-መስተዳድሩ፡-

(ሀ) የመስተዳድር ምክርቤት አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለምክርቤቱ በአጀንዳ የሚቀርቡ ጉዳዮችን ይወስናል፤

(ለ) የመስተዳድር ምክርቤቱን ስብሰባ ይመራል፤

(ሐ) ለመስተዳድር ምክር ቤቱ በአጀንዳ የቀረበ ጉዳይ በርዕሰ-መስተዳድር ጽህፈት ቤት መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው አጀንዳውን ለሌላ ጊዜ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 10

## የርዕሰ-መስተዳድር እና ካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት

1. የርዕሰ-መስተዳድር እና ካቢኔ ጉዳዮች ጽህፈት ቤት የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 63 መሠረት የርዕሰ- መስተዳድር እና የመስተዳድር ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ-መስተዳድሩ ሥልጣንና ተግባሩን ለማከናወን የሚረዱ ልዩ ልዩ ጽህፈት ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት

## የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ሥልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 11

### የወል ሥልጣንና ተግባር

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሠረት የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆነ እያንዳንዱ የአስፈፃሚ አካል መሥሪያ ቤት በሥራው መስክ:-

(ሀ) ሕግና ፖሊሲዎች ያመነጫል፣ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

(ለ) ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ያሰራጫል፤

(ሐ) የፌዴራልና የክልሉ ሕጐች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

(መ) በሕግ መሰረት ውሎችና ስምምነቶች ያደርጋል፣ ሠራተኛ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

(ሠ) የኤች አይ ቪ ኤድስ ተጠቂዎችና የአካል ጉዳተኞች እኩል ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ያመቻቻል፤

(ረ) በሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና የወጣቶችን ጉዳይ፣ የሕጻናት ጥቅምና ደህንነትን ያስጠብቃል፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን፣ የሠብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር መካተታቸውን ያረጋግጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

(ሰ) ክልላዊ የለውጥና የመልካም አስተዳደር ስራዎችን ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣ ዉጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፡፡

2. በየአስተዳደር እርከን የሚገኙትን የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያቤቶችን እና በማቋቋሚያ ሕጐቻቸው ተጠሪ የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያቤቶችን አፈጻጸም በበላይት ይመራል፣ ያስተባብራል፣አደረጃጀታቸው፣ የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን እና በጀታቸውን መርምሮ ለሚመለከተው የመንግስት አካል እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤
3. ተጠሪው የሆኑ የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶችን አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የልማቱ አጋዥ ሆነው መስራታቸውን ያረጋግጣል፤
4. በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤
5. ስለሥራው አፈፃፀም በየወቅቱ ለርዕሰ-መስተዳድሩ እና ለመስተዳድር ምክር ቤት ሪፓርት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 12

## የወል ተጠያቂነት

1. በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩት የመስተዳድር ምክር ቤት (ካቢኔ) አባላት በክልል መስተዳድር ምክር ቤት (ካቢኔ) ለሚያሳልፉት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለባቸው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሠፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ መስሪያ ቤት የተቋቋመበትን ዓላማ መሠረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ተለይተው የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

## አንቀጽ 13

## የባህልና ቱሪዝም ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገርቱን የቱሪዝም ልማት ፖሊሲ መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የቱሪዝም አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

2. በክልሉ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሚስፋፉበትን ሁኔታ ይፈጥራል፤ በግል ባለሃብቶች ለሚቋቋሙ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋሞች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤ ተቋማቱ የተወሰነላቸውን ደረጃ መጠበቃቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ የምክር አገለግሎቶችን ይሰጣል፤
3. አግባብ ካላቸው የክልሉ መስተዳድር አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የቱሪስት መስህቦችን ይመዘግባል፣ እንዲደራጁ፣ እንዲስፋፉ፣ እንዲለሙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፤
4. ስለ ክልሉ የቱሪዝም መስህቦችና የቱሪዝም ልማት መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀናጃል፣ ያሠራጫል፤
5. ቱሪዝም ነክ በሆኑ ጉዳዩች አግባብ ያላቸው የክልል መስተዳድሩን አካላት ያስተባብራል፤
6. በክልሉ የሚገኙ ቅርሶችን በሚመለከት የፖሊሲ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ኘሮጀክቶችን ይቀርፃል ይተገበራል ይከታተላል፣ ቅርሶች እንዲጠበቁና እንዲለሙ ያደርጋል፤
7. የክልሉን ነባር ብሔረሰቦች ባህልና ታርክ በተመለከተ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፣ ያስተዋዉቃል፣ የሚዳብሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
8. በክልሉ የባህል፣ የኪነ-ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
9. በክልሉ የሚገኙ ታሪካዊና ተፈጥሮአዊ ቅርሶች እንዲተዋወቁ፣ እንዲጠበቁ፣ እንዲታደሱና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
10. ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተለይተዉ እንዲታወቁ ጥናቶችን ያካሂዳል፣የሚወገዱበትን መንገድ ያመቻቻል፤
11. በክልሉ የፎቶግራፍና የስዕል ኤግዝቢሽኖች በማዘጋጀት የክልሉን ተፈጥሮአዊና ባህላዊን ቅርሶች እንዲታወቁ ያደርጋል፤
12. በዘርፉ የሚወጡ የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጐች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
13. በክልሉ ሙዚየሞችና የህዝብ ቤተ-መጽሐፍቶች እንዲደራጁና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
14. የቱሪዝም ክፍለ ኢኮኖሚ ሥራዎች በፌዴራሉና በክልሉ መንግሥት ፖሊሲዎች መሠረት መመራቱን ይቆጣጠራል፤
15. የቱሪዝም መስህቦችና ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ ሥራ ውጤቶች እንዲታወቁ ኤግዚቢሽን ያዘጋጃል፣ በሌሎች ክልሎች በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይም ይሳተፋል፤
16. የቱሪዝምን ልማት የሚመለከቱ ጥናቶችን ያካሄዳል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናክራል፣ ለሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፤

17.የቱሪዝም ልማት ሥራ ለማካሄድ ለሚፈለጉ የአገር ውስጥ ባለ ሀብቶት የምክር አገልግሎትና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ሥራቸዉን ይቆጣጠራል፣ያበረታታል፤

18. የቱሪስት አገልግሎቶች ደረጃቸውን የጠበቁ መሆኑን ይቆጣጠራል፣ደረጃቸው እንዲሻሻል የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

19. የቱሪስት መስህብነታቸው ለቱሪዝም ልማት ብቻ መዋል የሚገባቸውን ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣ የልማት ሁኔታቸውንም ይቆጣጠራል፣ ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

20. የቱሪስት መዳረሻ በሆኑ ሥፍራዎች የሚኖረው ኅብረተሰብ ከቱሪዝም ልማት ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር በሥራ ላይ ያውላል፤

21. በቱሪዝም ዋና ዋና መስህቦች አካባቢ የመሠረተ ልማት እንዲስፋፋ ጥናት ያደርጋል፣ ለሚመለከተው ክፍል ያስተላልፋል፣ ውሳኔ ሲያገኝ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

22.የክልሉ የቱሪዝም ሀብቶች እንዲጠበቁና እንዲታወቁ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የማስተዋወቅ ሥራ ያከናውናል፣የአገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲያበረታታ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

23.የክልሉ የተለየ የቱሪዝም አቅም የሆነውን የኤኮ-ቱሪዝም መዳረሻ ልማት ላይ ያተኮረ ሥራ ይሰራል፣ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆንም መስህቦቹ እንዲጠበቁ የግንዛቤ ማሻሻያ ሥራዎች ያከናውናል፤

24. የሆቴሎችና የቱሪዝም ሥራ ማሠልጠኛ ተቋሞች በክልሉ የሚስፋፋበትን ስልት ይቀይሣል ሥራቸውን ይቆጣጠራል፣ ይመራል፤

25. የመታሰቢያና የስጦታ ዕቃዎች ምርትና አቅርቦት ሊሻሻል ስለሚችልበት ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሠራል፣የምክርና የቴክኒክ ዕገዛ ይሠራል፤

26. የክልሉን ብዘሃ ህይወት ሀብት ተፈጥሮአዊና ሰዉሰራሽ ቅርሶች፣ ፓርኮችና መጠለያች ጥበቃ፣ቁጥጥርና ክትትል የሚመለከቱ ጥናቶች ያካሂዳል፣ ተከልለዉ እንዲጠበቁ እና ተገቢ የአጠቃቀም ሥረዓት እንዲኖራቸዉ ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ሕጎችንና ደንቦችን ያዘጋጃል፣ ሲናትቁም በሚመለከታቸው አካላት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ □ቆ□□ራል፤

27. የዱር እንስሳት ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ደንቦችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤ሕገ ወጥ የዱር እንስሳት አደን ይቆጣጠራል፣እርምጃ ይወስዳል፣እንዲወሰድም ያደርጋል፣ ስለዱር እንስሳት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፤
28. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣በስሙ ዉል ይዋዋላል፣ይከሳል ይከሰሳል፤
29. የክልሉን የስፖርት ኮሚሽን ስራዎች ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤ ለመስተዳደር ምክር ቤት መቅረብ ያለባቸውን ጉዳዮች እያቀረበ ያስወስናል፡፡
30. ዓላማዉን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## <u>አንቀጽ 14</u>

## <u>የግብርና ቢሮ</u>

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገሪቱን የገጠር ልማት ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና ስልቶች በክልሉ ውስጥ ያስፈጽማል፣ ይህንኑ መሠረት አድርጐ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል ሲፈቀድቅም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
2. ከአስገዳጅ ወይም ሕግ ከወጣላቸዉ የግብርና ምርቶች የግብይት ሥርዓት ዉጭ ለሆኑት ግብይቶች የህግ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከምርምርና ከማሠልጠኛ ማዕከላት ጋር ተቀናጅቶና ተሳስሮ ይሰራል፤ ድጋፍም ይሰጣል፤
4. የግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለተሠማሩ ባለሀብቶች ሙያዊ እገዛና ክትትል ያደርጋል፤
5. መደበኛ ተዛማጅ የእንስሳት በሽታዎችንና ፀረ-ሰብል ተባዮች በወረርሽኝ ሲከሰቱ አስቸኳይ የመከላከል ዕቅድ በማውጣት በክልሉ የሚገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችን እንዲሁም የኀብረተሰቡን አቅም በማስተባበር በባህላዊና ዘመናዊ መንገድ አደጋውን ይከላከላል፤

6. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን ለተጠቃሚዉ ህዝብ ለማስረጽ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች እንዲሰጥ ያደርጋል፣ ምርታማነት እንዲያድግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
7. አግባብ ካላቸዉ አካላት ጋር በመተባባር ለግብርናና ገጠር ልማት መፋጠን አስፈላጊ የሆኑ የእርሻ መሣርያዎች፣ ፀረ-ተባይ ኬሚካሎች፣የእንስሳት መድኃኒት፣ የብድር አገልግሎት እና ሌሎች የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አገልግሎት እንዲዳረስ ጥረት ያደርጋል፤
8. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቆጣጠር የአፈርና የውሃ ጥበቃ ሥራ ስልትን እየቀየሰ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
9. ቢሮው በሥሩ ለሚገኙ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ ዕፅዋት ክሊኒክ፣ የመካናይዜሽንና የገጠር ቴክኖሎጂ ኤጀንሲን፣ አፈር ምርምርና እንስሳት ላብራቶሪዎችንና ማዕከላትን ለግብርናው ዘርፍ አገልግሎት ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ይቆጣጠራል፤
10. የክልሉ የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ እንዲጠበቅ የተዘረጋ የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ስልት ቀይሶ ይሰራል፤
11. የነባር ብሔረሰብ ግብርና ዘይቤ በማጥናት የተፈጥሮ ሀብቱን አጠባበቅና ምርታማነትን ባገናዘበ መልኩ የግብርና ዘዴ ስልት በመቀየስ ብሔረሰቦች ከዘመናዊው የግብርና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
12. አነስተኛ የመስኖ ልማቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
13. የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያለማል እንዲለማ ያደርጋል፣ ከማናቸውም ጉዳት እንዲጠበቅ ያደርጋል የምርት ሰጪ ደኖች አጠቃቀም ይወስናል፣የምክርና የሥልጠና አገልግሎት ይሰጣል፤
14. ጥብቅ፣የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ደኖች የሚሰጡትን የሥነ-ምህዳር አገልግሎት በገንዘብ እንዲተመን በማድረግ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከሚመለከተው ጋር በመቀናጀት የደን ካርቦን ሽያጭ ኢንቨስትመንት እቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፣
15. የደን ምርምር እና ልማት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የምርምር፣ የግብዓት ማባዣ፣ የደን ዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር ማዕከላት እና ላቦራቶሪዎችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤
16. የደን ዕፅዋት ልማት እና ጥምር እርሻ እንዲለመድና እንዲስፋፋ ይሰራል፣ ያስተባብራል፣ ተስማሚ የሆኑ የደን ዛፍ ችግኞች እንዲዘጋጁ የቴክኒክ አገልግሎት እንዲዳረስ ጥረት ያደርጋል፤

17.በደን ዘርፍ የሚሰሩ ማህበራት እና ክበባት እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ፣ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

18.በመመናመን እና በመጥፋት ደረጃ የደረሱ የክልሉ ነባር አዝርዕት እና ሆሪቲካልቸሪ ዝርያዎችና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕዉቀት እንዳይበረዝ የመጠበቅ፣የማልማትና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲዉል ይሰራል፣ያስተባብራል፤

19.በመመናመን ላይ የሚገኙትን የዕፅዋትን እና ለማዳ የዉሃ ዉስጥ እንስሳትን እናደቂቅ አካላትን በመለየት የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

20. አደገኛና መጤ ወራሪ አረሞች አረሞች፣ በሽታዎችና ተባዮች ወደ ክልሉ እንዳይገቡ ተገቢዉን የመከላከያ ስልት ይነድፋል፣ተግባራዊ ያደርጋል፤በክልሉ ዉስጥ የሚገኙትንም እንዲወገዱ ጥረት ያደርጋል፣ከሚመለከታቸዉ ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ያስተባብራል፤

21. በክልሉ የእንስሳት ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ከሚመለከተዉ አካል ጋር የአሰራር ሥርአትን ይዘረጋል፣እንዲተገበር ያደርጋል፣ይከታተላል፤

22. የክልሉ አርሶ አደሮችን የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን መንገድ በመደገፍ ተግባራዊ ያደርጋል፤

23.የአርሶ አደሩ ምርቶችን ሳይባክኑ ገበያ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣የገበያ ትስስር ሊፈጥር የሚችሉበትን ስልት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመንደፍ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

24. ለአርሶ-አደሩና ለግል ባለሀብቱ የሚሰጥ የዘርፉ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ቀልጣፋና ጥራት ያለው፣ ተደራሽና ውጤታማ እንዲሆን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

25. በምርታማነታቸውና በሽታን በመቋቋም የታወቁ የሀገረሰብና የውጭ ዝርያ ያላቸው እንስሳትን ይለያል፣ ራንች በማቋቋም የዝርያ ማሻሻያ ሥራ ይሠራል፣ ያስፋፋል ፤

26. የእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ምርቶች ምርታማነትና ጥራት ደረጃ እንዲሻሻል ይሠራል፣ ቅድመና ድህረ- ምርት ቴክኖሎጂዎችን ያስተዋውቃል፣ ያስፋፋል ፤

27. የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት ማሳደጊያና ማሻሻያ ግብዓቶች አቅርቦትን ያመቻቻል፣ እንዲመረቱ ያደርጋል፣ በዘርፉ የሚሠማሩ አካላት አቅም ይገነባል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ ይሠርዛል ፤

28. የእንስሳት ክትባትና መድኃኒት አቅርቦት፣ የህክምና መስጫ መሳሪያዎች አያያዝ ዝውውር ሥርዓት ይዘረጋል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል፣ በህግ መሠረትም እርምጃ ይወስዳል ፤

29. የእንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት ይሰጣል፣ ከአጎራባች ክልሎችና ከፌደራል መንግሥት አካላት ጋር በቅንጅትና ትብብር ይሰራል፤
30. በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ ባለሀብቶችና አርሶ አደሮች የቴክኖሎጂ አቅርቦትና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል፣ የግብይት ትሥሥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ምርት እንዲያመርቱ ይደግፋል፣ ይከታተላል ይቆጣጠራል፣የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤
31. መከላከልን መሰረት ያደረገ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ይሰጣል፣ የእንስሳት በሽታዎች ምርመራ፣ አሰሳ፣ ጥናትና ቁጥጥር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የእንስሳት እንቅስቃሴን ይገድባል፣ ክልል አቀፍ የእንስሳ የበሽታ ቁጥጥር ስትራቴጂ ይነድፋል፣ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጃል ፤
32. ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ከበሽታ ነፃ የሆነና ጥራቱ የተጠበቀ ስጋ እንዲቀርብ በቄራዎች የስጋ ምርመራ እንዲካሄድ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ደረጃችውን የጠበቁ ቄራዎች በየከተሞች እንዲገነቡ ድጋፍ ያደርጋል፤
33. የእንስሳትን ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ የጥናትና ምርምር ተቋማትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ይመራል፡፡
34.በቢሮዉ ሥር ላሉ አስፈፃሚ አካላትና የልማት ተቋማትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ በተዋረድ ለዞንና ለወረዳ ግብርና መስሪያ ቤቶች ሙያዊ ድጋፍና እገዛ ይሰጣል፤
35.የግብርና ልማትን ለማስፋፋት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤
36. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣በስሙ ዉል ይዋዋላል፣ይከሳል ይከሰሳል፤
37. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 15

## የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ቀልጣፋ የግብይት ሥርዓትና ተገቢ የንግድ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፤

2. አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፣ የንግድ መዝገብ ያደራጃል፤
3. ተገቢ ያልሆነ የንግድ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችል የተሟላ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የንግድ ሕጎች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤
4. በሕግ መሰረት ለሸማቾች ጥበቃ ያደርጋል፣ የንግድ እቃዎችንና አገልግሎቶችን ሥርጭት ይቆጣጠራል፤
5. አግባብ ባለው አካል የዋጋ ቁጥጥር የተደረገባቸውን መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፤
6. አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤ ከተዘጋጀላቸው ደረጃ በታች ሆነው በተገኙት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤
7. የአገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክ ሥርዓት በአግባቡ መተግበሩን ይቆጣጠራል፤
8. የንግድና የዘርፍ የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤
9. በክልሉ የጠረፍ ንግድ ዙሪያ ተገቢዉን ፈቃድ ይሠጣል፣ያድሳል ይሰርዛል፤ተገቢዉን ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል፤
10. የግብይት ሥርዓትን በበላይነት ይመራል፣ የገበያ መሠረተ ልማት ያስፋፋል፣ የምርት ጥራት ቁጥጥር ያደርጋል፣ የብቃት ማረጋገጫ ይሠጣል፣ይከታተላል፣ በሕግ አግባብ እርምጃ ይወስዳል፤
11. የገበያና የንግድ ስራ መረጃዎችን በመሰብሰብ ፣ በማጠናቀር ፣ በመተንተንና በማሰራጨት ረገድ ተፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ፣ የገበያ ትስስር እንዲኖር ያደርጋል ፣
12. የክልሉን ምርቶችና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሚረዱ ቋሚ ኢግዚቪሽኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል ፣ ለሚያዘጋጁ አካላት ድጋፍና ፈቃድ ይሰጣል ፣ በሌሎች ክልሎች ኢግዚቪሽኖች ላይ ይሳተፋል ፣
13. የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርቡበት ስርዓት ይዘረጋል ፣ ይከታተላል ፣

14. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው ማናቸውም የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ የንግድ ፖሊሲ ፣ ህግና ደንብ መሰረት መከናወኑን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ ህጋዊነት ያለውና ስነ-ምግባር የተላበሰ የንግድ አሰራር እንዲከበር ያደርጋል ፣ ህገ ወጥ የንግድ አሰራሮችን ይከላከላል ፡

15. በየጊዜው የሚያሻቅበውን የዋጋ ንረት ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይነደፋል ህጋዊ አሰራርን መሰረት አድረጎ ተግባራዊ ያደርጋል፤

16. የንግድ ስርዓቱንና ሸማቹን ህብረተሰብ የሚጎዱ የተለያዩ ሕገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

17. አይነታቸውና የዋጋ ዝርዝራቸው በንግድ ሚኒስቴር የህዝብ ማስታወቂያ ክፍል የተገለጹት ወይም የሚገለጹት የንግድ እቃዎችና አገልግሎቶች በክልሉ ውስጥ ስለሚሰራጩበት፣ስለሚሸጡበትና ከቦታ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ይወስናል፣ እንደአስፈላጊነቱ እቃዎች ባለቁ ጊዜም እንዲተኩ ለነጋዴዎች መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤

19. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 16

## የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የገጠር መንገዶችን የሚመለከቱ አገር አቀፍ ፖሊሲዎችንና ህጎችን በክልሉ ውስጥ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፤
2. በክልሉ ውስጥ የገጠር መንገዶች የአዋጭነት ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት የገጠር መንገዶችን በተቀናጀ ሁኔታ ያለማል፣
3. በክልሉ ውስጥ የመንገድ አውታር የሚያድግባቸውንና የሚሻሻልባቸውን የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቁለትም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

4. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደው የገጠር መንገዶች ግንባታ ወጥነትና ፍትሐዊ ስርጭት እንዲኖረዉ ያደርጋል፤
5. የኢትዩጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሚያወጣቸውን አገር አቀፍ የዲዛይን ደረጃዎች በመከተል ለክልሉ ገጠር መንገዶች የሚያስፈልጉትን ዲዛይን በብቁ አማካሪዎች አማካኝነት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
6. የግንባታና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን በራሱ ሀይል ወይም በሌሎች አማካሪዎች አማካኝነት ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ውሎችን ይሰጣል፤
7. ከኢትዩጲያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመመካከር የክልሉን ገጠር መንገዶች በሚመለከት የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም መሣሪያዎችን ዲዛይን ያዘጋጃል፣ በአስፈላጊው የገጠር መንገድ ላይ ያኖራል ወይም እንዲተከሉ ያደርጋል፤
8. ለጋራ አገልግሎት እንዲውል በየትኛውም አካል ኃላፊነት የሚገነባውና የሚጠገነው ማናቸውም መንገድ ደረጃውን ጠብቆ ሲያገኘው መንገዱን ተረክቦ ያስተዳድራል፤
9. በህብረተሰቡ አማካኝነት የሚገነቡ የማህበረሰብ መንገዶችን በሚመለከት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ተፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍና የስልጠና አገልግሎት ይሠጣል፤
10. የገጠርም ሆነ የማህበረተሰብ መንገዶች አስተማማኝ የመንገድ ጥገና ዕቅድ ተዘጋጅቶላቸው ወይም ብቁ የጥገና ሀይል ኖሯቸው እንዲገነቡ የሚያስችላቸውን መመሪያ ያዘጋጃል፣ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
11. የገጠር መንገዶችን ከጉዳትና አግባብ ካልሆነ የመንገድ አጠቃቀም የተነሣ የሚከሰቱ እንቅፋቶችን ያስወግዳል፣ እንዲወገዱ ያደርጋል፤
12. በክልሉ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
13. በክልሉ ውስጥ መንገዶችን በራሱ ሀይል ይገነባል፤ ይጠግናል ወይም እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ መንግስት የልማት ድርጅቶች ወይም በግል የሥራ ተቋራጮች አማካኝነት እንዲገነቡ ወይም እንዲጠገኑ ያደርጋል፡፡
14. ለመንገዶች የሚውል ልዩ ልዩ የማቴሪያል ጥናቶችን ያከናውናል፤ እንዲያከናውኑ ያደርጋል፤ የግንባታ ማቴሪያሎች ለግንባታ ከመዋላቸው በፊት ጥራታቸውን በተመለከተ የብቃትና የጥራት ፍተሻ ያደርጋል፤ ያከናውናል፤
15. ለመንገዶች ግንባታና ጥገና ስራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ያሰለጥናል፤ እንዲሰለጥን ያደርጋል፤

16.የመንገዶችን ግራና ቀኝ አካባቢዎች ጨምሮ ለስራው የሚያስፈልገውን የመሬት መጠንና ሌሎች ሰዎችም ሆነ ድርጅቶች በዚሁ መሬት ሊጠቀሙ የሚችሉበትን ሁኔታ እያጠና ስልጣን ላለው የክልሉ መንግስት በማቅረብ ያስወስናል፤

17.ለመንገዶች ግንባታና ጥገና ስራ እንዲሁም ለካምፕና ለቢሮ አገልግሎት፤ለግንባታ ቁሳቁሶች ማምረቻ፤ለመሳሪያ ማስረፊያ፤ለመዳረሻ መንገዶች እንዲሁም አፈርና ድንጋይ ለማስወገድ የሚያስፈልገውን መሬት እና እንደ ድንጋይ፤አሸዋና አፈር የመሳሰሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች ያለ ክፍያ በነጻ ይጠቀማል፤ሆኖም መሬቱ የግለሰብ ይዞታ ከሆነ  ለመሬቱና በመሬቱ ላይ ላረፉ ወይም ለሚገኙ ንብረቶች በህግ መሰረት ካሣ ይከፍላል ወይም ትክ ይሰጥ ዘንድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ይረዳል፤

18.የተቋሙን ጋራዥ በበላይነት ያስተዳድራል; ለመንገድ ግንባታና ጥገና የሚያገለግሉ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎችን ይጠግናል፤

19. የትራንስፖርት አገልግሎቶች አቅርቦት በተቀናጀ መንገድ እንዲፈፀምና የክልሉን የልማት ስትራቴጂዎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያገለግል መደረጉን ያረጋግጣል፤

20. የትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት እንዲዘረጋና ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

21. የአገሪቱን የትራንስፖርት ፖሊሲዎች መሰረት በማድረግ በክልሉ በሚገኙ ውሃ አካላት ላይ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ያበረታታል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

22. በክልሉ የትራንስፖርት መሰረተ-ልማት አገልግሎት እንዲስፋፋ፣ እንዲሻሻልና እንዲጠገን ያደርጋል፤

23. በከተማ እና በገጠር የታክሲ አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የአሰራር መመሪያ ያወጣል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

24. በክልሉ ዉስጥ ለሚቋቋሙ የተሽከርካሪ ጥገና ጋራዦች፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትና ለተሽከርካሪ አመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ተቋማት የሚመሩበት የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፤ ይከታተላል አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤

25. ለሚሰጡ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ በጥናት ላይ ተመስርቶ ያወጣል፤ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

26. የሕዝብና የጭነት ማመላለሻ መናኸሪያዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣ የአሰራር ስርዓቱን ይዘረጋል፤

27. የመንገድ ትራንስፖርት ሕጎች መከበራቸውን ይከታተላል፣እርምጃ ይወስዳል፤
28. በክልሉ የመንገድ ደህንነት ካውንስል እንዲቋቋም ስልት ይቀይሳል፤
29. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ሲከሰት ወይም በሌሎች አስፈላጊ ምክንያቶች የንግድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎችን በአስፈላጊው ቦታና መስመር ደልድሎ ያሰማራል፣ ይከታተላል፤
30. ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመከላከል በቅንጅት ይሠራል፤
31. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
32. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 17

## የከተማ እና መሰረተ-ልማት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የከተማና የገጠር ትስስር እና የከተሞች የእርስ በርስ ትስስር እንዲጠናከር ስትራቴጂ ይቀይሳል ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. አግባብ ባለው ሕግ የክልሉን የከተማ መሬት አስተዳደር ሥርዓትን ያስፈጽማል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣የከተማ መሬት አቅርቦትና አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤
3. የከተማ ምግብ ዋስትና እና የሴፍትኔት ፕሮግራምን ያስተባብራል ከሚመለከታቸውም አካላት ጋር በመቀናጀት ይደግፋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ዘላቂነት ካለው የልማት ተግባር ጋርም ያስተሳስራል፤
4. የከተሞችን የደረጃ መመዘኛና ደረጃ ይወስናል፣ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
5. ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤
6. የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት እና ከድህነት ቅነሳ ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ በሚመለከት ጥናት ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያግዛል፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል፤
7. በከተሞች ዘመናዊ መሰረተ-ልማት እንዲስፋፋ ጥረት ያደርጋል፣ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት ያዘጋጃል፤
8. የክልሉን ከተሞች ፕላን ያዘጋጃል፣ አተገባበራቸውን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፤
9. በከተማ ፕላን ዝግጅት ለሚሰማሩ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል ደረጃቸውን ይወስናል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፤

10.ከተሞች የሚያመነጯቸውን ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች የሚወገድበትንና ውበት ያላቸው የመናፈሻ አገልግሎቶች የሚመሰረቱበትን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

11.በከተሞች ለሕዝብ ልማት ሲባል ለመንግስታዊ ፕሮጀክቶችና ለሌሎች አገልግሎቶች ለሚዛወሩ ይዞታዎችና ከይዞታቸው ለሚፈናቀሉ ሰዎች ካሳ የሚከፈልበት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

12. ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የለማ መሬት ያዘጋጃል፣ ለተገልጋይ ያቀርባል፣ የአቅርቦቱን ፍትሐዊነት ያረጋግጣል፤ የተላለፈ መሬት ሕጋዊነቱን ተከትሎ ለልማት መዋሉን ይከታተላል፣ ሕገ-ወጥ ግንባታዎችን ይቆጣጠራል፣ሕጋዊ ሥርዓትን ያስይዛል፤

13. የመሬትና የንብረት ዋስትና ካሳ ሥርዓት ይዘረጋል፤

14. በቴክኖሎጂ የተደገፈና ወጥ የሆነ የከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባና የአድራሻ መረጃ ሥርዓት በክልሉ ይዘረጋል፤

15. በከተሞች የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ ነዋሪው ህዝብ በተደራጀ አግባብ እንዲሳተፍ ለማስቻል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ የማስፈጸም አቅም ይገነባል፤ ያስተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

16. በክልሉ የሚካሄደውን የቤቶች ልማት ፕሮግራሞችን ይመራል፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠነ የመኖሪያ ቤት እንዲሰራ ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

17.የፌዴራልና የክልሉ መንግስት የግንባታ ኮዶች፣ ስታንደርዶችና ሕጐች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ የዲዛይንና የግንባታ ሥራዎችን ደረጃ ይወሰናል፤

18. በግንባታ ዘርፍ ለሚሰማሩ የምህንድስና ባለሙያዎች፣ አማካሪዎችና ሥራ ተቋራጮች ይመዘግባል፣ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

19.በክልሉ መንግስት ለሚገነቡ ሕንፃዎች የዲዛይንና የግንባታ ውሎች ስለሚይዟቸው የውል ቃሎችና የቴክኒክ መመሪያ ያዘጋጃል፣

20.በክልሉ መንግሥት ለሚካሄዱ ግንባታዎች የዋጋ ጥናት ያካሂዳል፣ የምህንድስና ግምት ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መሆኑን ያረጋግጣል፣

21.የኮንስትራክሽን ግብዓት በላቦራቶሪ እየተፈተሸ ለግንባታ አገልግሎት መዋሉን ያረጋግጣል፣

22.የክልሉን የኮንትራክሽንና የዲዛይን ሥራዎች ፍላጎት ያጠናል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

23.አግባብ ላለው አካል በሕግ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የኮንስትራክሽን ሥራ ደረጃዎች ያወጣል፣ መከበራቸውንም ይከታተላል፤

24.የኮንስትራክሽን ዘርፍን እንቅስቃሴ ይመራል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

25.በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካላት ለሚሰሩ ዲዛይኖች የማወዳደሪያ ዝክረ ተግባር ያዘጋጃል፤ የአማካሪ ደረጃ ይወስናል፣ የአማካሪዎችን ወርሃዊ የግንባታ ሂደት ሪፖርት ይገመግማል፣ የአገልግሎት ክፍያቸውን ያፀድቃል፤

26.በአማካሪዎች ወይም በሌላ አካል የተሰሩ ዲዛይኖችን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፣ ክፍያዎችን ያፀድቃል፤

27. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና የቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፤

28.የዘርፉን የሰው ሀብት ልማትና ደረጃዎች ዝግጅት ሥራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ የሚመለከታቸውን አካላትም ያስተባብራል፤

29.በመንግስትም ሆነ በግል ተቋማት በህንፃ አዋጁ በተካተቱ እና ወደፊትም በሚካተቱ ከተሞች ለሚገነቡ ህንፃዎች ዲዛይን ይገመግማል፣ የግንባታ ፈቃድ እና የመጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤

30.የህንፃ ሹም ጽህፈት ቤቶችን ያደራጃል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣ የግንባታ ግብአት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በጥናትና ምርምር ሥራው እንዲሳተፉ ያስተባብራል፤

31.በክልሉ የዲዛይንና የኮንስትራሽን ዘርፍ ለተሰማሩ አማካሪዎች፣ ኮንትራክተሮች እና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

32. በግንባታ ሥራ ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ግንባታዎች ጉልበት ተኮር እንዲሆኑ ያበረታታል፤

33.ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክልላዊ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት፣ መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

34.ክልላዊ የመንገድ መሠረተ ልማት ሥራዎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታነትንና ፍትሐዊ ተደራሽነትን መሠረት ባደረገ መልኩ መከናወናቸውን ይከታተላል፤

35.በክልል ደረጃ የከተሞች መዋቅራዊና መሠረታዊ ማስተር ፕላን ዝግጅትን ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

36.ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚለቀቅ የመሬት ይዞታ እና የንብረት ካሳ ቀመርና የነጠላ ዋጋ ያዘጋጃል፤

37.ከገጠር ወደ ከተማ የሚሸጋገሩ አካባቢዎችን በተመለከተ ስትራቴጂዎችንና፣ የልማት ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ስታንዳርዶችን ያወጣል፣ ይቆጣጠራል፤

38.አከታተምን በሚመለከት ጥናት ያካሂዳል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የተቀናጀ የአከታተም ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

39.ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤

40.የተመጣጠነ የከተሞች እድገትና የሕዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይተገብራል፤

41.የከተሞችን መሬት በቁጠባ እና በውጤታማነት መጠቀም የሚያስችል ዘመናዊ የአሠራር ስልት ይነድፋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

42.የከተሞችን ፈርጅ እና ሚና መወሰኛ መመዘኛ ያወጣል፤ የከተሞችን ጽዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፤ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

43.ከተሞች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ እና መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ በየደረጃዉ ላሉ የከተማ አደረጃጀቶች የአቅም ግንባታ እገዛ ያደርጋል፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን ያደርጋል፤

44.የከተማ አስተዳደሮችን የከተማ መሠረተ ልማት ሥራ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

45.ለዜጎች የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ለማሟላት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ በሚመለከታቸው አካላት ሲፀድቁም ተግባራዊነታቸውን ይደግፋል፤

46.የከተማ የምግብ ዋስትና ሥራን ያስተባብራል፤

47.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤

48. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 18</u>

## <u>የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ</u>

ቢሮ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ ሕግና ሥርዓት መከበሩንና የኅብረተሰቡ ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

2. በክልሉ የተጀመረዉን ልማት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል ሰላምና መረጋጋትን የሚያሰፍኑ ሰፋፊ የምክክርና ውይይት መድረኮችን ያዘጋጃል፤
3. በወሳኝ ክልላዊ ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ መግባባት እንዲመጣ በትኩረት ይሠራል፤
4. በአገሪቱና በክልሉ ሕገ መንግት የተቀመጡ የህዝብ ሰላም፣ ደህንነትና ነፃነት ጉዳዮች እንዲከበሩ እና እንዲረጋገጡ ፖሊሲዎችን ይተገብራል፣ የአመራርና የቴክነክ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡
5. የህዝቦችን ጥቅም ሊጎዱ የሚችሉ እና የሚቃጡ የሙስናና የወንጀል እንቅስቃሴዎችን መከላከል የሚያስችል ስልት ይቀይሳል፤ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤
6. ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ተገቢውን ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል፣ አደጋ ሲከሰት ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፤
7. በክልሉ ዉስጥ የሚኖሩ ዜጎች በተገቢ ሁኔታ ህጋዊ ጥበቃ እንዲያገኙ ድጋፍ ይሰጣል፤
8. ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፣ ህብረተሰቡን ወደ ግጭትና አለመረጋጋት የሚያመሩ ሁኔታዎችን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያመላክታል፤
9. የሕዝብና የአገር ሰላም እንዲጠበቅ አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የአጎራባች የክልል መንግሥታት አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤ ያለውን ቅንጅትና ትብብር ያጠናክራል፤
10. ከአጎራባች ክልሎች አዋሳኝ ቦታዎች፣ በክልሉ ዉስጥ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በከተማ አስተዳደሮች፣ በወረዳዎች እና በቀበሌዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችና ግጭቶችን በዘላቂነት እንዲፈቱ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ መፍትሄዎችን ያፈላልጋል፤
11. በክልሉ ዉስጥ ሰላም መጠበቁን ለማረጋገጥ ከአዋሳኝ የክልል መንግሥታት ጋር በኃይማኖትና እምነት ተቋማትና ተከታዮቻቸው መካከል ሰላም፣ መከባበርና መቻቻል እንዲሰፍን የሙያዊ ምክር፣ ዉይይት እና የአመራርና ድጋፎችን ያደርጋል፤
12. በአህጉራዊና እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ስጋት የሆነውን የኃይማኖት አክራሪነትና ጽንፈኛነት ችግሮችን በክልሉ እንዳይከሰቱ የመከላከል ሚናዎቹን ለሰላም፣ ለመረጋጋትና በፍቅር አብሮ የመኖር እሴቶች ለማሳደግ በሚችል አግባብ አጠናክሮ ያስፈጽማል፤
13. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላት ዴሞክራሲያዊ አመለካከታቸው እንዲዳብርና በሕገ-መንግስትና በሰብአዊ መብቶች ረገድ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ይሠራል፤

14. በየደረጃዉ የሚቀርቡ የሰላማዊ ሰልፍ ጥያቄዎችን በሕግ አግባብ መሆኑን ይከታተላል፤ የሚደረጉ ሰልፎችን ከተፈቀደለት ዓላማ ውጪ እንዳይሆን እና በሰላማዊ መንገድ መፈጸሙን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
15. የክልሉ የፀጥታ ኃይል ለአገር ሠላምና ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአገር መከላከያ ሠራዊት ጋር እንዲሰማራ ያደርጋል፤
16. የፀረ-ሠላም ኃይሎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ በዚህም የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ አሰራሮችን አጥንቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤
17. በክልሉ ውስጥ ባሉ አስተዳደር እርከኖች መካከል የሚነሱ የአስተዳደር ወሰን የማካለል ጥያቄዎች በሠላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን ይሰራል፤
18. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በአስቸኳይ በቁጥጥር ሥር ለማዋል እንዲቻል ሲታዘዝ የፀጥታ ኃይል ያሰማራል፤
19. የፀጥታ መደፍረስ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት በሚወስደው የመከላለል እርምጃ በሴቶች በህፃናት ላይ ጉዳት እንዳይርስ የጥንቃቄ እርምጃ ይወስዳል፤
20. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
21. ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 19

## ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፤
2. ለኢንቨስተሮችና በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
3. ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ መንደሮች የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መሰረተ ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤
4. ስለ ኢንቨስትመንት የወጡ ፖሊሲዎች እና ህጐች በክልሉ ውስጥ በትክክል መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፡ ይቆጣጠራል፤
5. የሚቀርቡትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች መርምሮ አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት አዋጆችና ደንቦች መሰረት የተደነገጉትን አስፈላጊ መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከዚህም የመነጨውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

6. የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች በኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ እና እንዲበርታቱ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፤ ዝርዝሩ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወስናል፤
7. በኢንቨስትመንት ህጐች ላይ የሠፈሩ ወይም ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጉዳ የሆኑ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ እንደአስፈላጊነቱ የሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል፣ ጥፋቱን የፈፀሙትን ሰዎች በህግ እንዲጠየቁ ያደርጋል፤
8. የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸውን ባለሀብቶች የሚያቀርቡት የማበረታቻ ጥያቄዎች የህጉን ድንጋጌዎች አሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጦ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣሌ፤
9. በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እድል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ መረጃዎችን ለባለሀብቶች ያሰራጫል፣ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶችን ያስተዋውቃል፤
10. ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚረዳ ኤግዚቢሽኖች፣ ስብሰባዎች፣ ሥልጠናዎች፣ ሴሚናሮችና የመሳሰለትን እንደአግባቡ በክልሉና ከክልሉ ውጭ ያካሂዳል፤
11. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አስመልክቶ ተገቢውን የምክርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤
12. በክልሉ ዉስጥ በሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አማራጭ እድል የተጠናቀሩ መረጃዎችን እንዲሁም ስለክልሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሪፖርቶችን ለክልሉና አግባብ ላለዉ የፌዴራል መንግሥት አካላት ያስተላልፋል፤
13. በክልሉ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ከባለሀብቶች፣ በመንግሥታዊ መ/ቤቶችና ከሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እና ትብብር እንዲኖር ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤
14. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌደራል መንግሥት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል ፍቃድ አግኝተው በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጨ ሀገር ባለሀብቶችን የሥራ ተግባራት ይከታተላል፤
15. በክልሉ ዉስጥ ያሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚዉሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ይከታታላል፣ይቆጣጠራል፤
16. የባለሀብቶች ፎረም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ይወያያል፤

17. የአነስተኛና የመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የዘርፍ ማሕበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣በህግ መሰረት ዉል ይዋዋላል፣በራሱ ሥም ይከሳል፣ይከሰሳል፤
19. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 20

## የፋይናንስ ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ በጀት የፊስካል ፖሊስ ማዕቀፍን መሰረት በማድረግ በየአመቱ በጀት ያዘጋጃል፣ በተፈቀደው በጀት መሰረት ክፍያ ይፈፅማል፣ የበጀቱን አፈፃፀም ያስተዳድራል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፡፡
2. ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ እርዳታና ብድር በማስተባበር ከክልሉ የልማት በጀት ዕቅድ ተጣጥሞ በስራ ላይ እንዲውል ያመቻቻል፣ ያቀናጃል፣ ይከታተላል፡፡
3. በክልሉ የሚታዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለማቃለል በስምምነት መሰረት የሚመጡ እርዳታዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ያስተዳድራል፣ ተጨማሪ እርዳታዎች ለማግኘች የተለያዩ ፕሮጀክቶች በመቅረፅና እንዲቀረፅ በማድረግ እርዳታ ለሚሰጡ ድርጅቶች ያቀርባል፡፡
4. በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ስራ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
5. በክልሉ ለመስራት የሚፈልጉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት/ የበጎ አድራጎት/ ድርጅቶች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን የፕላንና ልማት ስራን ከሚመራ ተቋም እና ከሚመለከተው መስሪያ ቤት በሚያገኘው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የብቃት ምዘና ያደርጋል፣ የሥራ ውል ይፈራረማል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፣ የፕላንና ልማት ስራውን ከሚመራው ተቋም ጋር በጋራ ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

6. የክልሉ የመንግስት አካላት የፋይናንስ ፖሊሲዎችን፣ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተከትለው መስራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ስለ ክልሉ ፋይንስ አያያዝና አጠቃቀም ጥናት እያደረገ የመፍትሄ ሀሳብ ያቀርባል፡፡
7. የክልሉን መንግስት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
8. የክልሉ መንግስት ከአገር ውስጥ ባንኮች የሚያገኘውን ብድር በክልሉ መንግስት ስም ተደራድሮ ይፈርማል፣ ብድሮችን እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፤
9. ዘመናዊ የበጀት አስተዳደር፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደር ስርዓት ይመሰርታል፣ ማስፈፀሚያ መመሪያ ያወጣል፣ የተቋማት ውስጥ ኦዲት ስርዓት ያጠናክራል፣ አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል፣ ይደግፋል፣ህጋዊ ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
10. የክልሉ መንግስት አክሲዮኖች፣ የሚተላለፉና የማይተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችና ሌሎች ተመሳሳይ የገንዘብ ሰነዶች ይይዛል፣ ይጠብቃል፡፡
11. የክልሉን መንግስት የፋይናንስና ንብረት ኢንስፔክሽን ያከናውናል፣ እርምጃ ይወስዳል እንዲወስድም ያደርጋል’
12. የክልል መንግስቱን የፋይናንስ ክንውን ይዞታና አስተዳደር የሚያስረዳ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ ለክልሉ መስተዳድር ካቢኔ ያቀርባል፤ለዓመቱ ከተዘጋጀው በጀት ሌላ ተጨማሪ በጀት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በተገቢው አካል ሲፈቀድ አዘጋጅቶ ያቀርባል፤
13. የክልሉ መንግስት አካል የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የክልሉ የመንግስት ሀብትና ንብረት ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል፤
14. የመንግሥት ተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም ስርዓት የተከተለ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
15. ግምታቸው በቢሮው ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት ሥር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶችን ይሸጣል፤
16. የመንግሥት ንብረት የማስወገዱ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፤
17. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
18. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 21</u>

## <u>የፕላንና ልማት ቢሮ</u>

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉን የረዥም፣የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፡፡
2. ከሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር በረዥም በመካከለኛና በአጭር ጊዜ ዕቅዶች ውስጥ የሚንፀባረቁ በክልሉ መንግስት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች እንዲጠኑና እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
3. የየሴክተሩን እቅድ አፈጻጸም እየተከታተለና እየገመገመ የተቀነባበረ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፤
4. የየሴክተሩን እቅድ አፈጻጸም እየተከታተለና እየገመገመ የተቀነባበረ ሪፖርት ያቀርባል እንዲሁም የአደረጃጀት ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን በመለየት ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመስራት ለመንግስት ያቀርባል፣
5. የክልሉን ሕዝብ ልማት በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል ጥናቶችን ያካሂዳል፤
6. የክልሉን የመካከለኛ ጊዜ የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊሲካል ማዕቀፍ ያዘጋጃል ያስፀድቃል፤
7. የክልሉን መንግሥት የካፒታል ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት ያካሂዳል፤ ይገመግማል፤ ያስፀድቃል፤
8. በክልሉ የታችኛውን የአስተዳደር ዕርከን ዓመታዊ የሀብት ማከፋፈያ ቀመር ያዘጋጅል፣ ለክልሉ ምክር ቤት እንዲጸድቅ ያቀርባል፣
9. የክልሉን የካፒታል ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፤ ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት አግባብነት ላላቸው አካላት ያቀርባል፣
10. የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ አፈፃፀም ጥናት ያካሂዳል፤ የአፈፃፀም ማሻሻያ ሃሳቦችን በማጥናት ለመንግስት ያቀርባል፡
11. የክልሉን የልማት ክፍተት እና የመልማት አቅም ጥናት ያደርጋል፤
12. የክልሉን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገፅታ ጥናት ያደርጋል፣
13. የክልሉን ዓመታዊ የሀብት /ኢኮኖሚ አካውንት/ ግመታ ሰነድ ያዘጋጃል፤ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፤
14. የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና መልክአ ምድራዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ትንተና በማድረግ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

15.የክልሉን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማት ስርጭትንና የመልክዓ ምድራዊ ገፅታን የሚያሳይ አትላስና ካርታ ያዘጋጃል፤

16.የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤቶች በሥራቸው ኃላፊነት የሚያመነጩትን ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ እንዲሁም ስታንዳርዱንና ጥራቱን ጠብቆ እንዲዘጋጅ ድጋፍ፣ ክትትል እና ኦዲት ያደርጋል ፣ በመረጃዎች ኦዲት ግኝት መሠረት ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

17.የክልሉን የመረጃ ክፍተት ለማሟላት የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ያከናውናል፤

18.የክልሉን የስታቲስቲክስ መረጃ ሥርዓት በማዘመን ለመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ድጋፍ ይሰጣል፤ ሥራውን ያስተባብራል፤ ይመራል፤

19.የሥነ-ህዝብ ጉዳዮችን በልማት ዕቅድ አካቶ ከመተግበር አኳያ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያስተባብራል፤

20.በሥነ-ህዝብ ጉዳዮች የማህበረሰቡንና አመራር አካላትን ግንዛቤ ለማጎልበት የሚያስችሉ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል፤

21.የሥነ ህዝብና ልማት ጉዳዮችን በተመለከተ የጥናትና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፤

22.በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙትን የሥነ ህዝብ ም/ቤቶችን በማጠናከርና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የ5 ዓመት የሥነ ህዝብ ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ለሥነ ህዝብ ም/ቤቱ በማቅረብ ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

23.በዕቅድና ፕሮጀክቶች ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዙሪያ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

24.በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ለመመዝገብና ለማስተዳደር በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 187 /2014 ዓ.ም መሰረት ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ተሰጥቶ የነበረዉ ተግባርና ሀላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት ሊሳተፉበት የሚችሉበትን የልማት መስክ እና የልማት ክፍተት ያለበትን አከባቢ በጥናት የመለዩት ተግባርና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ለፕላንና ልማት ቢሮ ተላልፏል፡፡

25. በክልሉ ለመስራት የሚመጡና ለፋይናንስ ቢሮ የሚቀርቡ ፕሮፖዛል እና ፕሮጀክት ከክልሉ የልማት አቅጣጫ አንፃር ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በጋራ ይገመግማል በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

26.በክልሉ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት አፈፃፀም የሚመለከታቸውን ሴክተር መስሪያቤቶችን በማስተባበር ክትትልና ግምገማ ያደረጋል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ጥፋት ከተገኘም የሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፡፡

27.ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 22

## የውሃ እና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ስለ ውሃ ሀብት ጥበቃና አጠቃቀም የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመከተል የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ የማሲፈጸሚያ ህጎችን ያመነጫል፤ ለተግባረዊነታቸዉ ይሰራል፣ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሸለቆዎችን፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ክምችትና ስርጭቶችን ያጠናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይመዘግባል፤ ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በሚካሄዱ ጥናቶች ይሳተፋል፣ በስራ ላይ ዕንዲውሉ የደርጋል፤
3. የክልሉ ውሃ ሀብት በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና ጥቅም ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤
4. የክልሉን የውሃ ሀብት በሚመለከት ማንኛውንም የውሃ ሥራዎች ለመስራትና በጥቅም ላይ ለማዋል ፍቃድ ይሰጠጣል፤ ከፍተኛ ደረጃ የውሃ ሥራ ፈቃዶችን በሚኒስቴር መስሪያ ቤት እንዲሰጡ ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፤
5. ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ለሚውል ውሃ የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ በተወሰነውም የጥራት ደረጃ መሰረት ፍሳሾች የተወሰነውን የጤናማነት ደረጃ በክልሉ ውስጥ በሥራ ለይ መዋሉን የከታተላል ይቆጣጠራል፤
6. ከማዕከል የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ጋር በመወያየት የውሃ ሀብት አጠቃቀምን ይወስናል፤ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ በሥራ ይተገብራል፤
7. በክልሉ በውሃ ሥራ ላይ የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ይተባበራል፤የሥራ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

8. የሜትሮሎጂና የኃይድሮ ጂኦሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል፤ መረጃዎችን ለቀጣይ ጥናት ያደራጃል፤
9. የውሃ ሀብት ልማት ጥናቶችን ያካሄዳል፣ዲዛይኖችን ይሠራል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
10. ንፁህ የመጠጥ ውሃ በክልሉ ከተሞችና የገጠር ሕብረተሰብ የሚዳረስበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ አቅም በፈቀደ መጠን ለቤት እንስሳት የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ያመቻቻል፤
11. የክልሉ ሕብረተሰብና ባለሀብቶች በውሃ ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ ተገቢውን የሙያና የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፤ በክልል ደረጃ የሚሠሩ የውሃ ሥራዎች ፈቃድ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
12. የመጠጥ ውሃ ተቋሞችን የእንክብካቤ መጠን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ በውሃ ልገሳቸው አቅም ላይ ጥናት ያካሄዳል፣ በጥናቱ ውጤት ላይ የተመሰረተ መፍትሔ ይሰጣል፤
13. በሴክተሩ ለሚሠሩ ተቋማትና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤
14. በዘርፉ በሥራ ላይ ለተሠማሩ አካላት የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይከታተለል፣ ይቆጣጠራል፤
15. ለኢነርጂ አጠቃቀም የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመከተል የክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ ሕጎችን ያመነጫል፣ ያወጣል፤ የወጡትንም በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
16. በክልሉ የሚገኙ ለመካከለኛ እና ከፍተኛ መስኖ ልማት ሊውሉ የሚችሉ ማንኛውም እምቅ የውሃ ሀብት ያጠናል፣ ለመስኖ ልማት እንዲውሉ ያደርጋል፤
17. በክልሉ የሚገኙ ማንኛውንም የውሃ ሀብት ያስተዳድራል፣ ለልማት እንዲውሉ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤
18. ውሃ ነክ ጉዳዩች የማማከር፣ የውሃ ሥራ ፈቃድና ሙያዊ ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ይሠጣል፤
19. በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የውሃ ሥራዎች የቁፋሮ ደረጃዎች ያወጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ሥራውም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የወጡ ሕጎችን የተከተለ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

20. በክልሉ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ለማዳረስ በነዳጅ ኃይል የሚሠሩ አነስተኛ የውሃ ኃይል ማምንጫ ጣቢያዎች ስለሚቃቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይልና ታዳሽ ኃይሎች የማመንጨትና የማሰራጨት ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤
21. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
22. የቢሮዉን አላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎችተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 23

## የማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ የማዕድን ሀብት ልማት እንዲስፋፋ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሌሎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ የክልሉን እምቅ የማዕድን ሀብቶች በዓይነት እና በመጠን ይለያል፤
2. በክልሉ ውስጥ የስነ-ምድር ጥናትና ምርምሮችን ያካሂዳል ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ጥናትና ምርምሮች በማካሄድ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌደራሉ መንግስት አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፡፡
3. የግልባለ ሃብቶች በማዕድን ሀብት ልማት ስራዎች በስፋት እንዲሳተፉ ያነሳሳል፤ የተለያዩ የፕሮሞሽን ስራዎችን በማከናወን ያበረታታል፤
4. ማዕድንን አስመልክቶ በሀገሪቱ የወጡ ህጎች በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ ስለመዋላቸው ያረጋግጣል፤
5. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የባህላዊ፣ በአነስተኛ፣ በልዩ አነስተኛ እና በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድ የማዕድን ሀብት ፍለጋ፤ ምርመራ፣ ግኝት፣ ምርት እና ይዞ የመቆየት ፍቃዶችን ይሰጣል፣ ያሳድሳል፣ ይሰርዛል፤
6. በክልሉ ውስጥ የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ማዕድናትን አመራረት፣ ግብይት እና አስተዳደር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
7. በባህላዊ እና አነስተኛ የማዕድን ማምረት ስራዎችን ይደግፋል፤ በክልል ውስጥ ዜጎች በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም ተደራጅተው በዚህ ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የስራ ዕድል እንዲፈጥርላቸው ያበረታታል፣ ፍቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

8. ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚከናወን ማናቸውም የማዕድናት ምርትና ዝውውር እንዲገታ አስፈላጊውን የቁጥጥር ስርዓት ይዘርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ በህገ-ወጥ መንገድ ተይዘው የተገኙ ማዕድናትን በአግባቡ ተጠብቆ ህጋዊ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
9. በማዕድን ሀብት ልማት ሂደት የሚገኘዉን ገቢ የሮያሊቲ፣ የመሬት ኪራይ እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ክፍያዎችን ይሰበስባል ፡፡
10. ማዕደንን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤
11. አግባብ ባላቸው የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ህጎች ከተፈቀደው ወሰን ሳያልፍ የክልሉን ኢኮኖሚ ለማሳደግና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በማዕድን ዘርፍ መንግስትን ያሳትፋል፤ ከባለሃብት ጋር እንዲቀናጅ ያደርጋል፤
12. የአምራች ማህበራት የፋይናንስ አቅም እንዲያድግ የብድር አግልግሎት የሚያገኙበት ምቹ ሁኔታ ያመቻቻል፤
13. ባህላዊ ወርቅ አምራቾች በማዕድን ህጎች፤ በስራአተ ጾታ፣ በአካባቢ ተጽዕኖ ላይ ስልጠና ይሰጣል
14. ባህላዊ የማዕድናት አምራቾች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ እንዲደራጁ ያመቻቻል፤ ይደፋል፤
15. በአምራች ማህበራት የአካባቢ ተጽእኖ የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን መልሶ የማከም ስራ እንዲስራ ያደርጋል፤
16. የቢሮው ዓላማ እና ተግባር ጋር ተዛማጅነት ያላቸዉን ትምህርታዊ የስልጠና ፅሁፎችን ያዘጋጃል፣ ያሳትማል፣ ያሰራጫል፤
17. የማዕድን ገቢን ለማዳበር የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል፤ የቢሮውን በጀትና የስራ ዕቅድ በማውጣት ሥራ ላይ ያውላል፣ ያስተዳድራል፤
18. የክልሉን ዕምቅ የማዕድን ሃብት በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች የማስተዋወቅ ሥራዎችን ይሰራል፤
19. የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ እንዲደረግ ከሚመለከታቸዉ መዋቅሮች ጋር በትብብር ይሰራል፤
20. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ የተመደበለትን በጀት፤ ሀብትና ንብረት ያስተዳድራል፤ የሥራ ውል ወይንም የአገልግሎት ውሎችን ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣
21. አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል ፤

## አንቀጽ 24

# የትምህርት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሰረት የክልሉን የትምህርት ዕቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
2. በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር ዕድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል፣ መሠረታዊ ትምህርትን ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፤
3. የክልሉ የትምህርት ጥራት በአገር አቀፍ ደረጃ የተወሰነለትን ስታንደርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤
4. የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና ስታንዳርድ ተከትሎና የክልሉንና የአካባቢውን ሁኔታዎች በማገናዘብ የክልሉን አንደኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ይተገብራል፣እንዲሁም በትምህርት ሚኒስቴር የሚዘጋጀዉን የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ሥራ ላይ ያዉላል፤
5. በደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያሠለጥናል፣ እንዲሰለጥኑም ያደርጋል፤
6. የመጀመሪያ ትምህርትን በነባር ብሔረሰቦች አፍ መፍቻ ቋንቋ ለመስጠት ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ይተገብራል፤
7. በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ፈተናዎችን ተከታትሎ ያስፈጽማል፣ በክልል ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣የምስክር ወረቀቶችንብቃት ያረጋግጣል፤
8. ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑ የመማሪያና ማስተማሪያ መፃህፍትና ሌሎች ድጋፍ ሰጭ ማጣቀሻ መጽሐፍት እንዲሁም ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፤
9. በክልሉ የሚገኙትን የትምህርት ተቋማትን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣ይከታተላል፣ እገዛ ይሰጣል፤
10. በክልሉ የትምህርት ተቋማትን ግንባታ ያካሂዳል፣ ያደራጃል፤ ደህንነታቸዉን ይከታተላል፤
11. የክልሉን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህትርት ቤቶችና ኮሌጆችን ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤
12. በድርጅቶችና ባለሀብቶች ለሚቋቋሙ እስከ ኮሌጅ ደረጃ ላሉ የትምህርት ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል፣ የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤
13. ለትምህርት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፣ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

14. ለክልሉ ነባር ብሔረሰቦች፣ ለሴቶች፣ ለህፃናት፣ልዩ ፍልጎት ትምህርት ለሚሹና ለጐልማሶች ለሚሰጡ የትምህርት አገልግሎቶች ልዩ ድጋፍ ይሰጣል፤
15. የክልሉ ትምህርት ፕሮግራም በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ያደርጋል፤
16. የትምህርቱን ሥራ ማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ጥናቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤
17. የትምህርት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ያጠናቅራል፣ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤
18. ለትምህርት ሥራ አስፈላጊ ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ኅብረተሰቡንና መያዶችን ሊያሳትፍ የሚችል ስልት ይቀይሳል፣ያስተባብራል፤
19. ከትምህርት ሥራ ጋር ተያያዥነት ባላቸዉ ጉዳዮች ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አብሮ ይሠራል፤
20. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
21. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 25

## የጤና ጥበቃ ቢሮ

የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገራቱን የጤና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ የክልሉ ህዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድና ፕሮግራም፣ ያዘጋጃል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
2. ስለህዝቡ ጤና አጠባበቅ የሚወጡ ህጐች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣ ደንቦችና መመያዎች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
3. በክልሉ ውስጥ በሚቋቋሙ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎችና ጤና ኬላዎች የምርምር የማሰልጠኛ ተቋሞችን ያደራጃል ያስተዳድራል፤
4. በሀገር ውስጥ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለማቋቋም የጤና ጣቢያዎች፣ የክሊኒኮች የላቦራቶሪዎችና የፋርማሲዎች ፈቃድ ይሰጣል በአገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን ደረጃ ጠብቀው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤
5. በክልሉ ውስጥ በህዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ይቆጣጠራል፤

6. ፍቱንነታቸውን የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶችን የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊ ህክምና ጋር ተዋህደው ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣የምዝገባ ደንብና ስርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤
7. ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት ክትባቶች እንዲሰጡና ሌሎች ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤
8. የህዝቡን ጤና ለመጠበቅ በሚደረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ይሳተፋል፣ በጠረፍ አካባቢ እንዲቋቋሙ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፤
9. የምግቦችንና መጠጦችን ለጤና ተስማሚነት ያረጋግጣል፣ የአገልግሎት ሰጭ ተቋሞችን የንፅህና አያያዝ ይቆጣጠራል፤
10. የጤና ፖሊሲውን መሰረት አድርጐ ሕዝቡ በበሽታ መከላከል ላይ በስፋት የሚሳተፉበትን፣ ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማጥፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፤
11. ስለሥራው አፈጻጸም ወቅታዊ መረጃዎችን እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድርና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያቀርባል፤
12. በክልል ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤
13. በጤና ዘርፍ በሁሉም ደረጃዎች ለሚገኙ የጤና ሠራተኞች አስተዳዳሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ኃይሎች ከጤና አገልግሎቱ ዓላማዎች አቅጣጫ ተገቢና ተከታታይ ሥልጠና ይሰጣል፤
14. በጤና አገልግሎት ሥርዓት በሁሉም ደረጃዎች የሚያስፈልጉና ደረጃቸውን የጠበቁ መድኃኒቶችና መሣሪያዎች አቅርቦት በየጊዜው ያሻሽላል፤
15. መድኃኒቶችን፣ የክትባት መገልገያዎችን፣ የክሕምና ቁሳቁሶችን፣ መማሪያዎችን በየአይነታቸውና እንደ አስፈላጊነታቸው ለጤና ተቋማት አቅርቦት ያሳድጋል። የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች መለዋወጫ አቅርቦት ጥገናና እንክብካቤ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤
16. በዋና ዋና የጤና ችግሮችና የጤና አገልግሎት ሥርዓቶች ተግባራዊ ምርምር ያስፋፋል፤
17. የተለመዱ የሕፃናት በሽታዎችን በተለይ የተቅማጥ የመተንፈሻ አካላት ተላላፊ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ባሉት የጤና መገልገያዎች በወቅቱ መጠቀምና የወጣቶች ልዩ የጤና ችግሮች ከዕድሜያቸው ጋር የተያያዙ የጤና ፍላጐቶች ላይ ትኩረት ማድረግ፤
18. አግባብ ያለው የሥራ ፈቃድ በመስጠት የግል የሕክምና ድርጅቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

19. በክልሉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ ህዝባዊና ኃይማኖታዊ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል ግንኙነት ያደርጋል፤
20. የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂክ ኘላን፣ እንዲሁም የሥራ ኘሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፀድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤
21. መግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ገንዘብና የተለያዩ ዕርዳታዎችን ያሰባስባል፤
22. በክልሉ የሚከናወኑ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የአባላዘር በሽታዎችን ቁጥጥር ሪፖርት ያጠናክራል፣ በአግባቡ ተንትኖ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
23. በክልሉ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ የሚደረጉ ጥናቶችን ያበረታታል፣ የተገኙትን ውጤቶችም ከፖሊሲው አኳያ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
24. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ የጤና አጠባበቅ ትምህርት በሕብረተሰቡ በስፋትና በጥራት የሚዳረስበትን መንገድ ይቀይሳል፣ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ በቅንጅት ተግባራዊ ያደርጋል፤
25. ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

## አንቀጽ 26

## የስራና ክህሎት ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የሚረዳ ከሀገራዊና ክልላዊ ሁኔታን ያገናዘበ የአጭርና የረጅም ጊዜ ፊዚካልና ፋይናንስ ዕቅድ አዘጋጅቶ በማፀደቅ ይተገብራል፣ ለዘርፉ የአስተዳደር መዋቅሩም ያወርዳል፣ አፈጻጸሙንም ይገመግማል፣ ለፈጻሚዎች ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ እንዲሁም ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤
2. የቢሮውን እና የቢሮውን የታችኛውን መዋቅሮች የሰው ኃይልና ተቋማዊ አደረጃጀት በጥናት በተደገፈ መልኩ ከወቅቱ የዘርፉ ስራዎች አኳያ እንዲደራጅ ይሰራል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤

3. የዘርፉን የልማት ስትራቴጂ በተገቢው ሁኔታ መተግበሩን ማረጋገጥ፣ በስትራቴጂው አፈፃፀም የሚከሰቱ ችግሮችን ጥናት ላይ ተመስርቶ መፍታት፣የውሳኔ ሃሳብ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፤
4. የዘርፉን ልማት ለማፋጠን የተዘጋጁ የድጋፍ ማዕቀፎች፣ የአቅም ግንባታ መርሀ-ግብሮችና እነዚህኑ ለማስፈፀም የተዘጋጁ ረቂቅ መመሪያዎችን መነሻ በማድረግ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም አፀትቆ ተግባራዊ ጸ□ርፉል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፤
5. በአገር አቀፍ ደረጃ የወጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሙያ ደረጃዎች ተግባራዊ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤
6. በሚወጣው አገር አቀፍ መመሪያ መሠረት የመካከለኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በክልሉ ውስጥ መደራጀታቸውን እና መተግበራቸውን ያረጋግጣል፤
7. የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲመሩባቸዉ የወጡና ወይም የሚወጡ መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ በሚገኙና የሚቋቋሙ የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባራዊ መደረጋቸዉን ይቆጣጠራል፣እንዲሁም የማሰልጠኛ ተቋማት እውቅና አሰጣጥ በሚመለከት የሚወጡ አገር አቀፍና የክልሉ መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናዎች የሙያ ብቃት ምዘናና ማረጋገጫ ማዕከል እንዲደራጅ ያደርጋል፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ክህሎት ምዘና አፈፃፀም መቆጣጥርን ጨምሮ በክልሉ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት መኖሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
9. የቴክኒክ ሙያ ትምርትና ሥልጠና ተቋማት የቴክኖሎጂ ሽግግርና የፈጠራ እንዲሁም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፈልፈልያ ማዕከላት እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፤
10. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ከማምረቻና ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር ተቀናጅተው የሥራ ላይ ልምምድ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር አስፈላጊውን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
11. በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ እንዲቻል የድህረ ሥልጠና ክትትል ያደርጋል፣ የድህረ ሥልጠና ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

12. በክልሉ ውስጥ ለሚካሄዱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የደረጃ ብቃት ማረጋገጫና እውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ በሚወጣው ደንብ መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑትንና የሥልጠና ጥራት ላይ ችግር ያለባቸውን ተቋማት የዕውቅና ፈቃድ ይሰርዛል፤

13. የክልሉን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች በበላይነት ያስተባብራል፣ እንዲሁም ቦርዶች በክልሉ ኮሌጆችና በተቋማት ደረጃ በሕግ መሠረት መቋቋማቸውን ይከታተላል፣ አደረጃጀታችውና አስተዳደራቸውን እያጠና እንዲሻሻል ለሚመለከተዉ ያቀርባል፣ የሥልጠና አካሄዳቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

14. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የምርት ማዕከላትን በማቋቋምና የገቢ ማዳበሪያ ሥርዓት በመዘርጋት የውስጥ ገቢያቸውን የሚያዳብሩባቸዉን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

15. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የግል ባለሀብቶች በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና ኮሌጆች ጋር የጠነከረ ግንኙነት ይዘረጋል፣ ያበረታታል፣ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

16. በክልሉ ከሚገኙ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ከሀገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ መሰል ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የልምድ ልውውጥ ያደርጋል፣የጋራ ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይፈራረማል፤

17. በማሰልጠኛ ተቋማት መካከል የክህሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የተግባራዊ ምርምር ውድድር እና ሲምፖዚየም በማዘጋጀትና እንዲዘጋጅ በማድረግ ዘርፉን ያበረታታል፤

18. ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ አሰልጣኞች፣ አመራሮች፣ ባለሙያዎች አቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፤ በዘርፉ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ ይፈጥራል፣

19. በክልሉ ለዜጎች የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ የሚችሉ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ፀጋዎች ልየታ በጥናት እንዲለዩ ያደርጋል፣ ውጤቱን በየደረጃው እንዲተገበር ያስተባብራል፤

20. በክልሉ የአስተዳደር መዋቅሮች የሥራ ፈላጊ ዜጎች ምዝገባ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሥራ ፈላጊዎች ልየታ ያደርጋል፤

21. □□ር□ን ውጤማነት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማስቀጠል በእሴት ሰንሰለት ጥናት ላይ መሠረት ያደረገ የኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት መፍጠርና ለአንቀሳቃሾች ክፍተት ላይ የተመሠረተ የሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ማትረ□፤

22. ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በዘርፉ ልማት ስትራቴጂዎች መሠረት ያደራጃል፣ ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ እንዲሁም በሕግ አግባብ ይሰርዛል፤
23. ለሚደራጁ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት እንዲሁም በሥራ ላይ ላሉ የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ብቃታቸውን የሚያሻሽልና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል የሙያ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
24. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ማደራጀትና ማጠናከር፣ አገልግሎቶቹን በአግባቡ መስጠት የሚያስችል የተሻሻሉና አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት የማዕከላቱን አቅም ይገነባል፤
25. በዘርፉ ለተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች በቂ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ በፍትሃዊነት መተላለፉን ያረጋግጣል፣ ለተላለፈለት ዓለማ ስለመዋሉ ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
26. ለኢንተርፕራይዞች በየአስተዳደር መዋቅሩ በሚገኙ የገበያ አማራጮች የአካባቢ፣ የሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ የገበያ ትስስር እንዲያገኙ ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ እንዲሁም የንግድ ትርዒትና ባዛሮችን በየአስተዳደር መዋቅሩ እንዲዘጋጁ ያስተባብራል፣ በተዘጋጁ ሀገር አቀፍ መድረኮች ኢንተርፕራይዞች አንዲሳተፉ ያመቻቻል፤
27. በየአስተዳደር መዋቅሩ ለሚገኙ ነባርና አዲስ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ ምክርና የኦዲት አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል፣ይቆጣጠራል፤
28. ሥራ ፈላጊዎች እና ኢንተርፕራይዞች የቁጠባ ባህል ለማዳበር በቅድመ እና ድህረ ቁጠባ እንዲሁም ብድር አሰጣጥ እና አመላለስ ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፤
29. በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ስተራቴጂዎች መሠረት የደረጃ ዕድገት ሽግግር ሥራዎችን ያከናውናል፣ እውቅናም ይሰጣል፤
30. □ተለጸ□ ሚዲያዎችን በመጠቀም በየደረጃው ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂን ለሕብረተሰቡ በስፋት የማስተዋወቅና የግንዛቤ መፍጠር ሥራዎችን መሥራት እንዲሁም ዘርፉን የሚመለከቱ የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤
31. በክልሉ ወጥ የሆነ የዘርፉ የመረጃ ልውውጥና አጠቃቀም ሥርዓት ያደራጃል፣ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸውን መረጃዎች ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ለውሳኔ በሚረዳ መልኩ ያደራጃል፣ እንዲሁም ሕጋዊ በሆነ መልኩ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

32. ዘርፉን በሚመለከት ከሚሰሩ ወይም ሊያግዙ ከሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የጋራ መግባቢያ ሰነድ በመፈራረም ይሰራል፤
33. የዘርፉን ልማት ሊያግዙ የሚችሉና ቁልፍ ማነቆዎችን ለመለየት የሚያስችል ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ያከናውናል፤
34. የሀገሪቱን የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ፖሊሲዎች በክልሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
35. አሰሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በክል ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤
36. የሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የሥራ ሁኔታዎች ደረጃቸውን የመከላከል ዘዴዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
37. በክልሉ የሚቋቋሙትን የሠራተኞችና የአሰሪ ማህበራትን ይመዘግባል፤ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤
38. ህብረት ስራ ድርድሮችና የሥራ ክርክሮች በህግ በተዘረጋው ስርዓት ተከትለው ስርዓት እንዲያገኙ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈጽሙ ጥረት ያደርጋል፤ የህብረት ስምምነቶችንም ይመዘግባል፤
39. በክልሉ በሚገኙ የግል እና የመንግስት የልማት ደርጅቶች የሰው ኃይል የስራ ስምሪት አገልግሎትን ይሰጣል፤
40. የንብረት ባለቤት የመሆን፣ውል የመዋዋል፣በስሙ የመክሰስና የመከሰስ  መብት እና ግዴታ አለው፤
41. ቢሮው የሚሰራቸውን ስራዎች አስመልክቶ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሕግ አግባብ ለሶስተኛ ወገን በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤
42. ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 27

## የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የሴቶች፣ የሕፃናት እና የወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤
2. ሴቶችና ወጣቶች በክልሉ በኢኮኖሚ፣በፖለቲካና በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችላቸዉ እድሎች የተመቻቸላቸዉ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ሴቶችና

ወጣቶች እንደ ፍላጎታቸዉና እንደ ችግሮቻቸዉ ተደራጅተዉ ለመብቶቻቸዉ እንዲታገሉን ችግሮቻቸዉን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ሁኔታዎችንም ያመቻቻል፤

3. በክልሉ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶች፣ የሕፃናት እና የወጣቶች ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
4. በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ መድሎዎችን ፣ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል ፣ አፈጻፀሙን ይከታተላል ፣ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሰራል፤
5. በክልል ደረጃ የሴቶች የልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
6. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲመቻች ያደርጋል፣አፈጻፀሙን ይከታተላል፤
7. የሴቶች እና የወጣቶች አደረጃጀቶችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፣ የሥልጠና አገልግሎት የሚሰጥበትን አሰራር ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፤
8. የእናቶች የኑሮ ሁኔታ ስለሚሻሻልበትና የሕፃናት መብትና ደህንነት ስለሚጠበቅበት ሁኔታ ያጠናል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፤
9. በክልሉ ሴቶችንና ሕጻናትን የሚመለከቱ አገራችን የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች አፈጻፀም ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፤
10. ሴቶች በክልሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸው ሊያረጋግጥ የሚያስችሉ ዕድሎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያመቻቻል፤
11. በክልል ደረጃ የሴቶች፣ የሕፃናት እና የወጣቶች መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ የፖሊሲ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ ስልት በመቀየስ ለተግባራዊነቱም የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣ያስተባብራል፤
12. የሴቶችና የህፃናት ተሳትፎ ለማጉልበትና በኅብረተሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር የሚረዱ የግንዛቤና የንቅናቄ መድረክ ያመቻቻል፤

13. በአገር አቀፍና በክልል ደረጃ የወጡት የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ በክልሉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ስልት ይቀይሳል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
14. የህፃናት መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ ይሠራል፣ የሚመለከታቸው አካላት ያስተባብራል፤
15. በክልሉ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሴቶችና ህፃናትን በሚመለከት ጉዳዮች ዙሪያ አብሮ ይሰራል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ አፈፃፀማቸውን ይገመግማል፤
16. በክልሉ ሕግ አውጪ፣ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚው የመንግስት አካላት አደረጃጀት ውስጥ ሴቶች በውሳኔ ሰጪ ቦታዎች ላይ በሚገባ መወከላቸውን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፤
17. በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙት ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ችግር ለመቅረፍ የሚረዱ ጥናቶችን ያጠናል ወይም ያስጠናል፣ ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን በመቅረጽ ፈንድ ያፈላልጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
18. እያንዳንዱ ሴክተር መስሪያ ቤት እቅድና ሪፖርት ሥርዓተ-ጾታ ያገናዘበ መሆኑን ይገመግማል ወይም ያስገመግማል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከል እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
19. የሴቶችን፣ የህጻናትንና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመላክቱ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰበስባል ያደራጃል፣ ይተነትናል በሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤
20. የተደራጁ ሴቶችና ወጣቶች ተገቢውን የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፎች እንዲያገኙ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
21. ሴቶችና ወጣቶችን በላቀ ደረጃ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ጥናትና ምርምሮችን በማከናወን የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችንና ማዕቀፎችን ይቀርፃል፣ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤
22. በክልሉ የመንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የወጣቶች ጉዳይ እንዲካተቱ ስልት ይነድፋ፣ይገመግማል፣ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
23. ወጣቶች በመልካም ሥነ-ምግባር እንዲታነፁ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላትን እንዲገነቡ ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፤
24. የወጣቶች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር በማሳደግ የበጎነት አድራጎት ተግባር የክልሉ ባህል እንዲሆን ይሰራል፣ ያስተባብራል፤
25. የሀገሪቱን የማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎች በክልሉ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

26. በተለያዩ ጡረታ ማህበራዊ ዋስትና ዕቅድ የሚሸፈኑ የክልሉ ሠራተኖች በመብታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል እርምጃዎችን ይወስዳል፤
27. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባባር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያን፤ አካል ጉዳተኞች እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
28. የማህበራዊ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን ህብረተሰብ ያስተባብራል፤ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፤
29. የቤተሰብ ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የጋብቻ ስርዓት ለመንከባከብ የሚወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤
30. የማህበራዊ ችግር ተጋላጭ እና ከስደት ተመላሽ ዜጎችን የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ተጠቃሚነትን ያሳድጋል፤
31. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ዉል ይዋዋላል፣በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፤
32. የቢሮዉን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎችተግባራትን ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 28</u>

## <u>የመሬት እና ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ቢሮ</u>

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለመሬት ተጠቃሚ አርሶ አደሮች ወይም ድርጅቶች የይዞታ የመጠቀሚያ መሬት ትክክለኛ ስፋት በመወሰን በካዳስተር □ተ□ቹ□ □ብተር ለመስጠት የአሰራር ማንዋል በማዘጋጀት አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ □ቆ□□ራል፤
2. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉን የመሬት ዓይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፣ ያስተዳድራል፣ አጠቃቀሙን ይወስናል፣ ይቆጣጠራል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል፣ እንደ አስፈላጊነቱ መረጃዉን ለተጠቃሚዎች ይሰጣል፤
3. መሬት በተለያዩ ምክንያቶች እንዳይጎሳቆል ወይም ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን የመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎች እንዲያደርጉ ትምህርት ይሰጣል፣ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ግዴታቸውን በማይወጡ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

4. በመሬት የመጠቀም መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች/ድርጅቶች/ የያዙትን መሬት የመጠቀም መብት በውርስ/በስጦታ/በኪራይ/ የሚያስተላልፉበትን እና ሌሎች መሬትን ለማስተዳደር የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ይቀርጻል፣ ሲፈቀድም ያስፈጽማል፤
5. የግል ባለሃብቶች በመሬት ላይ የልማት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የአጠቃቀም እቅዳቸውን እየገመገመ ያፀድቃል፣ በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
6. የክልሉን የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር መረጃዎችን ለማደራጀት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክልላዊ የመረጃ ቋት ይመሰርታል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ትንተና እያካሄደ ወቅታዊ ማስተካከያዎችን ያደርጋል፣ በአካባቢና በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ፍላጎት ላላቸው ተጠቃሚዎች ዝግጁ ያደርጋል ያሰራጫል፤
7. የክልሉ የልማት ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ዘላቂ የመሬት አጠቃቀምን መሰረት አድርገዉ እንዲተገበሩ ክልል አቀፍ መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፤
8. በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ላላቸው አካላት የቴክኒክ ምክርና ድጋፍ ይሰጣል፤
9. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የሕግ ማዕቀፎችን ያዘጋጃል፣ የሚመለከተው አካል ሲያፀድቅም በበላይነት ይተገብራል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፣ ዝርዝር የአሠራር ሂደቶችን ፣ ማንዋሎችን እንዲሁም ሌሎች የሥነ-ምድር መረጃ ማሰባሰቢያና ማሰራጫ ቅፃቅጾችን በማዘጋጀት ያሰራጫል፤
10. ለህዝብ ጥቅም ሲባል ይዞታውን እንዲለቅ ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ ተመጣጣኝ ካሣ ማግኘት እንዲችል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፣ አፈጽጸሙንም ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤
11. ከገጠር መሬት የይዞታና የመጠቀም መብት ጋር ተያይዛ የሚነሱ አቤቱታዎች፣ አለመግባባቶችና ቅሬታዎችን በማጣራት ተገቢውን አስተዳደራዊ ምላሽ ይሰጣል፤
12. አዲስ የይዞታና የመጠቀም መብት በመለየት በህጉ መሠረት የመሬት አቅርቦት ያመቻቻል፣ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያስፀድቃል፣ አስፈላጊውን ውል እንዲይዙ ያደርጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ ግዴታቸውን በማይወጡ ተጠቃሚዎች/ ባለይዞታዎች ላይ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤
13. በገጠር መሬት ላይ ለሚሰማሩ አልሚ የግል ባለሃብቶች በሕጉ መሠረት የመሬት አቅርቦት ያመቻቻል፣ ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ያስፀድቃል፣ አስፈላጊውን ውል እንዲይዙ ያደርጋል፣ የመጠቀም መብት ያስከብራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን

አፈጻጸማቸውን በመከታተል ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣ ግዴታቸውን በማይወጡ ተጠቃሚዎች/ባለይዞታዎች ላይ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

14. በግል፣ በጋራ፣ በወልና በመንግስት የገጠር መሬት ይዞታዎች ላይ መረጃ በማሰባሰብ፣ በማጠናከርና በመተንተን ጥራት ያለውና ወቅታዊ መረጃ ለተጠቃሚው ያደርሳል፣ ክልላዊ የገጠር መሬት የካዳስተር እና ሌሎች መሬጃዎች ቋት በመፍጠር ለተገልጋዩ እንዲደርሱ ያደርጋል፣ የማሳን የመረጃ ለውጥ በየጊዜው በመከታተል በመመዝገብ ወቅታዊ ያደርጋል፤

15. የገጠር መሬት ምዝገባ ሥርዓት ይዘረጋል፣ይተገብራል፣አፈጻጸሙንም ይደግፋል፣ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የሚከናወኑ ሥራዎች በበላይነት ያቅዳል፣ ይፈፅማል፣ ይከታተላል፣ሪፖርቱንም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ያደርጋል፤

16. ከአከባቢያዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ አገልግሎት አንፃር ጠቄሜታቸው የጎሉ የገጠር መሬቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጥናት በመለየት የይዞታና የመጠቀም መብት ያረጋግጣል፤

17. ለክልሉ ልማትና ዕድገት የሚያስፈልጉ የገጠር መሬት የካዳስተር ቅየሳ፣የካርታና ሌሎች የሥነ ምድር መረጃ ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ጥናት ያደርጋል፣ወቅታዊ ማስተካከያዎችን እያደረገ ተግባራዊ ያደርጋል፤

18. የገጠር መሬትን ለተሻለ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ተጠቃሚነትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በተለያዩ ደረጃ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ያዘጋጃል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በሚወጣው የአጠቃቀም እቅድ መሠረት ግዴታቸውን በማይወጡ ተጠቃሚዎች ባለይዞታዎች ላይ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤

19. የአባላትን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ የተለያዩ ማህበራትን ያደራጃል፣ የአባላት ቁጥር በየጊዜው እንዲጨምር ትምህርትና ቅስቀሳ ያደርጋል፣ አቅም ይገነባል፣ ይከታተላል፤ ያጠናክራል፡፡

20. ዓለም አቀፍ የህብረት ሥራ መርሆችን መሰረት በማድረግ የተደራጁ ማህበራት በክልል ብሎም በአገር ዓቀፍ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተሳትፈፎአቸው እንዲያድግ አደረጃጀታቸውን፣ አሰራራቸውን እና አገልግሎት አሰጣጣቸውን በማዘመን ቀጣይነታቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል፡፡

21. በክልሉ ውስጥ የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የኅብረት ስራ ማህበራትን የማደራጀት፣ አቅም የመገንባት እና የማጠናከር ሥራ ይሰራል፤ የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ከማሳደግ

አንፃር መደበኛና ወለድ አልባ የገጠር ፋይናንስ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራትን እንዲደረጁ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ያጠናክራል፡፡

22. በህግ አግባብ የተደራጁ ማህበራትን ይመዘግባል፤ ህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርቴፊኬት ይሰጣል፤ ይሰርዛል፤ የኢንስፔክሽን ሥራ በመስራት የአሰራር ክፍተቶች ካለ ወቅታዊ ማስተካከያ ያደርጋል፡፡
23. የፖሊሲ ሃሳቦች ያመነጫል፤ የምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ ስትራቴጅዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ ይፈፅማል፣ ይተገብራል፡፡
24. የኅብረት ሥራ ማህበራትን ሊጠቅሙ የሚችሉ እና በአባላት ተሳትፎ የሚሰሩ የልማት ፕሮጀክቶች እንዲዘጋጁ በማድረግ የአፈፃፀም ስትራቴጂ እና ቅደም ተከተል እንዲወጣ ምቹ ሁኔታን በመፍጠር በተግባር ላይ መዋላቸውን ይገመግማል፤ይከታተላል፡፡
25. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ አያያዝ ውስጥ የቁጥጥር ስርዓት እንዲጠናከር ሂሳብ የማስተካከል አገልግሎት ሙያዊ እገዛ በመስጠት የገንዘብ እና የንብረት ብክነትን ይከላካል፤ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ተከታትሎ ወቅታዊ የሂሳብ ምርመራ ያደርጋል፤
26. በማህበራት ሀብትና ንብረት ላይ ጥፋት ከመድረሱ አስቀድሞ በሚያደርጋቸው የሂሳብ ምርምራ ውጤት መሰረት ለማስመለስ ጥረት ያደርጋል፤ተገቢው ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ያሉ የኅብረት ስራ ማህበራትም ውክልና ሲሰጡትም የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
27. በክልሉ ውስጥ ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት የብቃት ደረጃ ማረጋጋጫ እውቅና አሰጣጥና ምዘና በመስራት የደረጃ ማረጋገጫ ዕውቅና ይሰጣል፤
28. ዘርፉ የሚጠይቀውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በትምህርት ዝግጅትና በሙያ ያበቃል፣የአጭር እና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች እንዲያገኙ ያመቻቻል ከሚመለከታቸው የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋርም በቅንጅት ይሠራል፡፡
29. ኅብረት ሥራ ማህበራት በነፃ ገበያ ተወዳዳሪና ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገትም የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ወቅታዊና አስፈላጊ የገበያ መረጃዎች እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
30. የክልሉን የመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖችን መረጃዎችን ለማደራጀት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክልላዊ የመረጃ ቋት ይመሰርታል፣ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ትንተና እያካሄደ ወቅታዊ ማስተካከያዎችን ያደርጋል፣

31. በገጠር የተደራጁ ዩዩኒኖችና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የግብርና ምርቶችን ከህገ-ወጥ ደላሎች በመከላከል ምርቱን በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፣

32. በከተማም ሆነ በገጠር የተደራጁ ዩዬኒኖችና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት የፍጆታ ዕቃዎችን፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን፣ የግንባታ ዕቃዎችን እንዲሁም የአባላትን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ሌሎች ሸቀጣ ሸቀጦችን ለአባላትና ለአካባቢው ሸማች ማህበረሰብ እንዲያቀርቡ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣

33. የተደራጁ ዩኒዩኖችና መሰረታዊ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎችን (ፀረ-ተባይ፣ ፀረ-አረም፣ የሰብል ተባይ መከላከያ ከረጢቶች እና ልዩ ልዩ የአትክልት ዘሮችን ለአባላትና ለአርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ያቀርባል፣ የተመረተውን የአትክትልት ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ እንዲያቀርቡ እገዛ ያደርጋል፣

34. ዩኒዩኖችና መሰረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት መጋዘን፣ የመሸጫ ሱቅ፣ የምርት መሰብሰቢያና መረከቢያ ማዕከላት የተሟላ እንዲሆን እገዛ ያደርጋል፣ ምርታቸው ላይ እሴት ለመጨመር የሚያስችል የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን በስፋት እንዲያቋቁሙ በማድረግ ለክልሉ ስራ ፈላጊ ወጣቶች የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ያደርጋል፣

35. የህብረት ስራ ማህበራትን የግብይት ፋይናንስ ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ የተለያዩ የብድር ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት ብድር ያስፈቅዳል፣ ከአቻ ማህበራትና ከተለያዩ አበዳሪ ተቋማት ጋር የፋይናንስ ትስስር ይፈጥራል፣

36. የኑሮ ውድነትን ለመከላከል ለሸማች ማህበራት የፍጆታ ዕቃዎች አቅርቦት የሚውል የተዘዋዋሪ ፈንድ ከሚመለከታቸው አካላት ያስፈቅዳል፣ ብድሩ ሲፈቀድም ገንዘቡ እንዳይባክን ይቆጣጠራል፣ ተከታትሎ የማስመለስ ሥራ ይሰራል፣

37. ከግብርና ምርምርና ከግብርና ቢሮ ለምርጥ ዘርነት የሚለቀቁ የተለያዩ መስራች ዘሮችን የህብረት ስራ ማህበራት በክላስተር እርሻ እንዲያባዙ ያግዛል፣ ጥራቱ የተረጋገጠውን ዘር ይሰበስባል፣ ለአባላትና ለአባቢው አርሶ አደሮች በሚፈቀድላቸው የዋጋ ተመን መሰረት በወቅቱ እንዲሰራጭ ያደርጋል፣

38. የኅብረት ስራ ማህበራት ተደራሽነት በገጠርም ሆነ በከተማ ለማስፋፋት እና ለማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና በማዘጋጀት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ሠራተኞች እና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፡፡

39. በየደረጃው አስፈላጊ የሆኑ አደረጃጀቶች እና የአሰራርር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፡፡

40. አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራቸው በኩል የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ብድር እንዲያገኙ የምርት ውጤቶችን እና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ የገበያ ትስስር በመፍጠር በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤
41. መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራትና ዩኒኖዬች የሚዋሄዱበት እና በሚለያዩበት ወይም በሚፈርሱበት ጊዜ በህግ አግባብ እንዲፈጸም አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
42. የህብረት ስራ ማህበራትን የሚመለከቱ ህጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፡፡
43. የራሱን ዕቅድ እና በጀት ያዘጋጃል፡፡ በጀቱ ሲፈቀድም ያስተዳድራል ስራ ላይ ያውላል፡፡
44. የተቋሙን የሰው ኃይል ያሟላል፣
45. የኅብረት ስራ ፌደሬሽኖች፣ ዩኒዬኖችና መሠረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት በሚሰሩበት ሥራ ወይንም አገልግሎት ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፤ይከሰሳል፤
46. ከአጎራባች ክልሎችና ከፌደራል መንግሥት አካላት እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅትና በትብብር/በመተባበር/ ይሰራል፣
47. በኅብረት ሥራ ማህበራት ለሚደራጁ ሴቶችና ወጣቶች በቁጠባ እና ብድር አቅርቦት ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የግብይት ትሥሥር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፡፡
48. የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭትን በኅብረት ስራ አማካኝነት ለህብረተሰቡ የምርት ግብዓት ማቅረብ፤ ማሰራጨት፤ ብድር ማስመለስ፣ መቆጣጠር እና አፈፀሙንም ተከታትሎ በመገምገም የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፤

## አንቀጽ 29

## ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በፌዴራል የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራተጂዎች እና ህጎችን ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ፈጻሚ ባለቤት እንዲኖራቸው በማድረግ አቀናጅቶ በበላይነት ይመራል፣ ለተግባራዊነታቸው የሚያስፈልጉ የሕግ ማዕቀፎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
2. በክልሉ የልማት መርሃ ግብር የሚካተቱ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ይከታተላል፣ በበላይነት ያስፈጽማል፣ ውጤታማነታቸውንና ውስንነታቸውን ይገመግማል፣ የሚሻሻሉበትንም አማራጭ ያቀርባል፤
3. በክልሉ መንግስት የሚነደፉ የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት እቅዶችን መነሻ በማድረግ አጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የሚጠይቁትን የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት፣ የአሠራር ሥርዓትና ሌሎች የአቅም ግንባታ ፍላጐቶች ላይ ጥናት በማድረግ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ፖሊሲ ነክና ስትራቴጂያዊ እርምጃዎችን የሚመለከት ሀሳብ ያመነጫል፤
4. በፌዴራል ደረጃ ተቀርጸው በሥራ ላይ የሚውሉ የተለያዩ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የሥልጠና ፕሮግራሞች በክልሉ በተገቢው አኳኋን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
5. በክልሉ የተዋቀሩ አስፈጻሚ አካላት አንድ ወጥ የሆነ፣ ተደጋጋፊና የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት፣ የመረጃ አያያዝ፣ ልውውጥና አጠቃቀም፣ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት እንዲኖር ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
6. የአቅም ግንባታ ሥራን ለማፋጠን የሚያስችሉ ተቋማት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ያጠናል፣ በአቅም ግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማትን ይገመግማል፣ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉበትን ስልት ይቀይሳል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ፕሮግራሞች እንዲነደፉ ያደርጋል፤
7. የግልና የሕዝብ ተቋማትን፣ የማህበራትንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ያስተባብራል፤
8. ተጠሪነታቸዉ ለቢሮው የሆኑ መስሪያ ቤቶች የትኩረት አቅጣጫዎች፣ የተሻሻሉ የአሠራር ሥርዓቶች እንዲሁም ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት አስፈላጊውን እገዛ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ በበላይነት ይመራል፤
9. የመንግስት መስሪያ ቤቶችን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የሚያድግበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ለዚህም ተገቢውን እገዛ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

10. ሥራ ላይ የዋሉ  የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ለመተግበር ከፌዴራል መንግስት እና መሰል ተቋማትና ከሌሎች ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣ በጋራ በመገናኘትም ፕሮግራሞቹ የበለጠ የሚዳብሩበትን፣ የሚሻሻሉበትንና በክልሉ የሚኖረውን ግንዛቤ የሚዳብርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
11. በክልሉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት መሠረት የተለያዩ የአገር ውስጥ እና ውጭ አገር የትምህርትና ሥልጠና እድሎች በአግባቡ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤
12. የክልሉን መንግስት መስሪያ ቤቶች በልማት ድርጅቶችና በግሉ ዘርፍ የሰዉ ሀብት ልማት በቀጣይነት የሚለማበትና ጥቅም ላይ የሚዉልበት  ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራይነቱን ይከታተላል፤
13. በክልሉ ለዲሞክራሲ ሥርዓትና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ እገዛ የሚያደርጉ ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ለተግባራዊነታቸዉ ያስተባብራል፤
14. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች አስተዳደርን በሚመለከት የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጐች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
15. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ በሚያወጣቸዉ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን መሰረት በክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ በሚገኙ የሥራ መደቦች ላይ ምደባ ይሰጣል፤
16. ለመንግስት ሠራተኞች የተፈቀደውን የደመወዝ እስኬል፣ የልዩ ልዩ አበሎች፣ ክፍያና ሌሎች የሥራ ሁኔታዎችን በሚመለከት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
17. ከሲቪል ሰርቪሱ አገልግሎት አሰጣጥና የልማት ስራዎች ጋር በማያያዝ የሠራተኞች የደመወዝ ክፍያ፣ ማትጊያና ማበረታቻዎች እና የዕርከን ጭማሪ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሠራተኛን ተነሳሽነት፣ ጥረትና የስራ አፈጻጸም ውጤታማነትን መሠረት ባደረገ መልኩ የሚፈጸምበት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።
18. በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አቀጣጠር፣ አመዳደብ፣ ደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ ዝውውር እና የዲሲፕሊን ጉዳዮች በሕጉ መሠረት መፈጸማቸዉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲሁም ያረጋግጣል፤
19. የክልል መስተዳድሩን የመንግስት ሠራተኞች ዝርዝር ሁኔታ መዝግቦ ይይዛል፣ ስታትስቲካዊ መረጃዎች ያጠናቅራል፣ ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ያስተላልፋል፤
20. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች ከጡረታ ዕድሜ ክልል በላይ አገልግሎታቸው እንዲራዘም ለሚቀርቡ ጥያቄዎች  የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

21. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች ከሥራ ለማሰናበት በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤
22. ከክልሉ የመንግስት ሠራተኞች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በሚቀርቡ የይግባኝ አቤቱታዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ያልተፈጸሙ የሲቪል ሰርቫንት የይግባኝ ቅሬታዎችን ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች ያስተላልፋል፤
23. ለክልሉ መንግስት ሠራተኞች የሥራ ውጤቶች መመዘኛ መመሪያ ያወጣል፤ ሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤
24. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች የሚደረጉ የጊዜያዊ ሠራተኞች ቅጥርን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፤ አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፤
25. የክልሉ መንግስት ሠራተኞች የፌዴራል ሕጐችን በመተርጐም ረገድ ያጋጠሙ ችግሮችን ለፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ያስተላልፋል፣ በትክክለኛ ትርጓሜያቸዉ መሠረት መተግበራቸዉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤
26. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልል መንግስቱን አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም በመገምገም የማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራና ሠራተኛ መገናኘቱን ያረጋግጣል፤
27. በመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራሞች፣ ልዩ ልዩ ጥናቶች፣ የማስፈጸሚያ ሕጐች፣ በተቀናጀ መንገድ የሚተገበሩበትን ስልት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
28. የክልሉ መሥሪያ ቤቶች በስትራቴጂያዊ አመራር ዘይቤ የሚመሩበትንና የተቀናጀ የማሻሻያ ፕሮግራም አፈጻጸም ስልት የሚዳብርበትን ሥርዓት በመቀየስ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤
29. ልማታዊ መልካም አስተዳደር ለማረጋገጥ መንግስት፣ ህዝብንና ልማታዊ ባለሀብቱን አቀናጅቶ ያስተባብራል፤
30. የለዉጥ ፕሮግራሞች፣ ጥናቶችና ውጤቶችን አፈጻጸም በወቅቱ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያቀርባል፣ እንዲሁም በክልሉ አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የማሻሻያ ጥናቶችን በመለየት የጥናት አፈጻጸም ቅደም ተከተል ያወጣል፣ መረጃዉንም በሥርዓት አደራጅቶ ይይዛል፤
31. በአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ረገድ የአገር ውስጥና የውጭ ተሞክሮዎችን በማጥናት ጠቃሚ ልምዶች ከክልሉ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

32. የክልሉ የካይዘን ፍልስፍና አስተሳሰብ ያሰርጻል፣ ውጤታማ እንዲሆንም ተቋማዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ ክትትል ያደርጋል፤
33. የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል ምርጥ ልምዶች በመውሰድና በመቀመር ከየዘርፉ ባህሪ ጋር በማጣጣም አገልግሎቶች ጥራት ያላቸው፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆኑ ይሰራል፣ በሌሎች ተቋማትም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
34. የሲቪል ሰርቪሱ የአገልግሎት አሰጣጥ ግልጽኝትና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን አቅም በፈቀደ መጠን የዜጎች ቅሬታ በህጋዊና እና በፍትሀዊነት የሚስተናገድበት የተጠናከረ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
35. የሰው ሀብት ህጎችን ተፈጻሚነት ለመቆጣጠር የሚከናወነው የጠቅላላ ምርመራ /ኢንስፔክሽን/ ስራ በግኝት መልክ የሚታዩ ግድፈቶች የሚስተካከልበትን መንገድ ለባለቤቶቹ በግብረ-መልስ ያሳውቃል፣ተግባራዊ በማያደርጉ ተቋማትም ላይ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
36. የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ ዕቅድ አፈጻጸም ምዘና የተጨባጭ የአፈጻጸም ውጤት ደረጃ መገለጫ እንዲሆን፤እንዲሁም ለመንግሥት ሠራተኞች የሚሰጥ ዕውቅናም ሆነ ተጠያቂነትን በቀጥታ ከሥራ አፈፃፀም ውጤት ጋር የተያያዘ እንዲሆን ይሰራል፡፡
37. በሐሰተኛ የትምህርት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃዎች ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ ወይም ሌላ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት የሚሞክሩ የመንግስት ሠራተኞችን ማስረጃዎች በማናቸውም ጊዜ ይፈትሻል፣ ያጣራል፣ በሌላ በሚመለከተው አካል እንዲጣራ ያደርጋል፣ ሐሰተኛ ሆኖ ሲገኝ በሚመለከተው አካል አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ እና የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
38. ከፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የሚወርዱ ሀገር አቀፍ ይዘት ያላቸው መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን እና አሰራሮችን ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ማሻሻያዎችን ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፡፡
39. በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ዘዴን በመጠቀም ዜጎች በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚኖራቸውን ግብረ-መልስም ሆነ ቅሬታ የሚያቀርቡበት ሥርዓት ይዘረጋል፣
40. ዓላማዉን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

## <u>አንቀጽ 30</u>

## <u>የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ</u>

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የክልሉ መንግስት ቃል አቀባይ እና ዋነኛ የመረጃ ምንጭ በመሆን ይሰራል፤ በክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ የክልሉን አቋም ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፤ በየደረጃው ያለው የመረጃና የመረጃ ልውውጥ መዋቅር ለየተመደበበት የክልሉ አደረጃጀት በቃል አቀባይነት ኃላፊነቱን የሚወጣበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

2. የክልሉን ስራዎች ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ ሁሉንም አይነት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ግብዓቶችን እና ውጤቶችን በብቃት ፣ በጥራትና በስፋት በመጠቀም የመንግስት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ተደራሽ በማድረግ በህዝብና በመንግስት መካከል የሁለትዮሽ ተግባቦት እንዲፈጠር ያደርጋል፤
3. የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን መሰረት በማድረግ ማህበረሰቡን ተደራሽ የሚያደርጉ አጀንዳዎች በማዘጋጀት የተግባቦት ስራን ይሰራል፤
4. የመንግስትን ፖሊሲ፣አቋምና ዕቅድ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉና የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያሳድጉ ንቅናቄዎችን ይፈጥራል፤አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፤ ለማህበረሰቡ ያሳውቃል፤
5. ሀገራዊና ክልላዊ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ ህብረ-ብሔራዊ አንድነትን፣ሀገራዊና ክልላዊ መግባባትን፣ የዴሞክራሲ ባህል መጎልበትን እንዲሁም ሁለንተናዊ እድገትን ማረጋገጥ እንዲቻል በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሚዲያዎችን ያስተባብራል፤ ከሀገር አቀፍና አለማቀፍ ሚዲያዎች ጋር በትብብር ይሰራል፤
6. በክልሉ መንግስት አስፈጻሚ ለሆኑ ሴክተር መ/ቤቶችና ተቋማት የህዝብ ግንኙነት ዘርፎች ለስራዎቻቸው የሚሆኑ የአሰራር መርህ፣ ደረጃና ስርዓት በማውጣት እንዲተገበር ያደርጋል፤
7. በክልሉ ለሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች የህዝብ ግንኙነት ዘርፎች፣ ለዞን ፣ ለከተማ አስተዳደር እና ለወረዳ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን መዋቅሮች የሁለትዮሽ የተግባቦት ስራን ለማከናወን የሚያስችል አቅም ይገነባል፤
8. ከህዝብ ሰላምና ደህንነት ፣ ከታላላቅ ሀገራዊ እና ክልላዊ ክንውኖች ፣ ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ፣ ከህዝብ ንቅናቄ ሥራዎች ፣ ከግጭቶች ፣ ወዘተ ጋር በተያያዘ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ ከሚመለከታቸው አካላት በዳሰሳ ጥናት እና በህዝብ አስተያየት ቅኝት መረጃ ይሰበስባል፣ይተነትናል፣ ድምዳሜዎችን ለሚመለከታቸው ያሳውቃል እንዳስፈላጊነቱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፣ ለውጡን ይከታተላል ፤ ፤

9. በሀገራዊ እና በክልላዊ ጉዳዮች ላይ በመመስረት የተለያዩ ዜናና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤ ይገመግማል ፤ ለክልልና ለሀገር አቀፍ ሚዲያዎች ይልካል፤ ተደራሽነታቸውን ይከታተላል፤የተለያዩ ኒው ሚዲያዎችን በመጠቀም ተደራሽነታቸው ስፋት እንዲኖረው ያደርጋል፤
10. የመንግስትን እቅዶችና ተግባራትን ወደ ህዝብ ለማድረስ የሚረዱ ሀገራዊ እና ክልላዊ ሁነቶችን እንዲሁም ህዝባዊ ውይይቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል ፣ ይደግፋል፤ በተደራጀ አግባብ ይመራል ያስተባብራል፤
11. የክልሉን መንግስት ስራዎችና አጠቃላይ ክልላዊና ሀገራዊ ወቅታዊ መረጃዎችን ለክልሉ ህዝብ፣ በሀገርና በውጭ ሀገር ለሚገኙ አካላት ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል የኒው ሚዲያ መስተጋብሮችን አሰራር ይዘረጋል፤ አደረጃጀቶችን ይፈጥራል፤ በበላይነት ያስተዳድራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤
12. የመረጃ አርካይብና ዶክመቴሽ ስራ ይሰራል፤ የመንግሰት መረጃዎች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤ የመረጃ ነጻነት አዋጅ እንዲተገበር ያደርጋል፤
13. በክልሉ ወቅታዊ እና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይሰጣል፤ የሚመለከታቸው ሴክተር መስራያ ቤቶች ተቋሙ በሚያወጣው መርሃ ግብር መሰረት ማብራሪያዎችን እና መግለጫዎችን እንዲሰጡ ያደርጋል፤
14. በክልሉ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ውስጥ ያሉ የኮሚዩኒኬሽን ኃላፊዎች በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት በሜሪት እንዲመደቡ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
15. በክልሉ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ክልሉን በሚመለከት የሚወጡ የሚዲያ መረጃዎችን ዳሰሳ በመስራት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር እንዲሁም እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤ ምላሽ እንዲሰጥበት ያድረጋል፤ ከዳሰሳ መረጃዎች በመነሳትም አስፈላጊውን የኮሙዩኒኬሽን ስራ ይሰራል፤
16. ሀገራዊ እና ክልላዊ መግባባትን ለመፍጠር፣ ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለመረጋገጥ እና የክልሉን ገፅታ ለመገንባት እንዲቻል የተለያዩ የተግባቦት እና የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ያከናውናል፤ ለዉጤታማነቱም በክልሉ የሚገኙ ተጽህኖ ፈጣሪ አካላትና ግለሰቦች እንዲሁም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የድርሻቸውን እንዲወጡ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ያስተባብራል፤
17. ልዩ ልዩ የህትመትና የኦዲዮ እና አውዲዮ ቪዝዋል ውጤቶችን ያዘጋጃል፤ በክልሉ መንግስታዊ ተቋማት የሚከናወኑ የፎቶ ግራፍ፣ የኦዲዮ ቀረፃና የዓርማ እና የህትመት

ዲዛይን ተግባራት ፖለቲካዊ፤ ህጋዊ፣ ማህበረሰባዊና የሞራል ጥያቄ የማያስነሱ መሆናቸውን እና ከተቀመጠላቸው ዓላማ ጋር የተገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣል፤ አገልግሎት ይሰጣል፤

18. በክልሉ ውስጥ የኮሚዩኒኬሽንና የሚዲያ መሰረተ ልማት የሚጠናከርበትን፣ የሚስፋፋበትን ፣ በተገቢው ቴክኖሎጂና ብቃት ባለው የሰለጠነ ባለሙያ የሚደራጅበትን ሥርዓት ይቀይሳል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
19. የውጪ ማስታወቂያ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፤ የውጭ ማስታወቂያ ስራ ለመስራት ለሚፈልጉ ማናቸውም ዜጎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፤
20. አግባብ ባለው ሕግ ስለ ውጭ ማስታወቂያ መልካም ሥነ-ምግባር፣ የህብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች የሚያከብር፣ የአገርን እና የክልልን ክብርና ጥቅም የሚያስጠብቅ ይዘትና አቀራረብ ያለው መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡
21. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ሕጋዊ ተግባራትን ያከናውናል፤

## <u>አንቀጽ 31</u>

## <u>የገቢዎች ባለስልጣን</u>

መስሪያ ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፡-

1. በክልሉ ውስጥ የታክስ ሕጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን ያስከብራል፣ ያስፈጽማል፤
2. በሕግ ተለይተው በክልሉ መንግስት እንዲሰበሰቡ የተመደቡትንና ከፌዴራሉ መንግስት በሚሰጠው ውክልና መሠረት በክልሉ መንግስት እውቅና የፌዴራልንና የጋራ ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤
3. በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመሥርቶ ጥናቶችን በማካሄድ የክልሉን የገቢ መሠረት ያሰፋል፤ በታክስ አስተዳደሩ የሚከሰቱ ችግሮችን በማጥናት እንዲፈቱ ያደርጋል፤
4. በክልሉ ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለውን የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም አፈፃፀም በባለቤትነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤
5. የታክስ ሕጎችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትንና በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ እና ከወንጀል ሕግ ጋር የማይገናኙ ሰነዶችን ይመረምራል፤

6. ታክስ ከፋዩ ኅብረተሰብ ታክስ በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን እንዲያዳብርና መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ እንዲረዳ በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል፤ የታክስ አስተዳደር ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማፍራት የሚያስችለውን የሥልጠናና የሙያ ማሻሻያ ስልቶች ይዘረጋል፤
7. በክልሉ ውስጥ ዘመናዊ የታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤ በመስኩ የግልፅነትና የተጠያቂነት መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ታክስ ነክ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤
8. በክልሉ ውስጥ ለሚገኙት ታዳጊ ከተሞች እና ማዘጋጃ ቤቶች ለሚሰበስቧቸው ገቢዎች ባለስልጣኑ ሁሉአቀፍ የሙያ ድጋፍ እና የተሟላ አቅም እንዲኖራቸው የአሰራር ስልጠና፤ክትትልናድጋፍ ይሰጣል፤
9. ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ያሰባስባል፤ ያጠናክራል፤ እነዚህኑ በመጠቀም ታክስ ይወስናል፤ ይሰበስባል፤የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ማውጣትና ማሻሻል ሲያስፈልግ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ለክልሉ መንግስት አቅርቦ ያስወስናል፤
10. ለታክስ ከፋዩ አማራጭ የታክስ መክፈያ ተቋማትን ያመቻቻል፤
11. የመሥሪያ ቤቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤ የስራ እንቅስቃሴዎቹን በሚመለከት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርቶችን ያቀርባል፤
12. ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ጸድቆ በሚወጣ ልዩ የባለስልጣኑ የሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ያሰናብታል፤
13. ባለስልጣኑ በክልሉ መንግሥትና በወረዳ/ከተማ አስተዳደር ስልጣን ሥር የሚወድቁትንና የጋራ የግብር እና ታክስ መሠረቶችን አይነትና ብዛት ይለያል፤ በእነዚሁ አካላት መካከል የሚከፋፈልበትን ቀመር ያዘጋጃል፣ ለክልሉ መንግሥት አቅርቦ ያስወስናል፤
14. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በሥሙ ይከሳል፣ይከሰሳል፤
15. ዓላማዎችን ለማስፈጸም የሚረዱሌሎች በህግ የተፈቀደ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 32

## የክልሉ ፍትህ ቢሮ

የክልሉ ፍትህ ቢሮ አንዱ የክልሉ መንግስት አስፈጻሚ አካል ሆኖ የራሱ ማቋቋሚያ አዋጅ ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች መዋቅር እና ኃላፊዎች

### አንቀጽ 33

### የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆኑ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋሙ አስፈጻሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች እንደሁኔታው በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር ደረጃ ተሻሽለው እንደገና ሊቋቋሙ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ይወሰናል፤
2. የአስተዳደር ምክር ቤት አባል የሆኑ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ተጠሪነት ለዋና አስተዳዳሪውና ለአስተዳደር ምክር ቤቱ እንዲሁም በየደረጃው ላሉ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች ይሆናል፤
3. ለአስፈፃሚ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በየአስተዳደር እርከን ላሉት መስሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚ ይሆናል፤
4. እያንዳንዱ የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች፤ እንዲሁም የሥራ ሂደት ባለቤቶች እና ሠራተኞች ይኖሩታል፤
5. ተቀራራቢ ተግባር ያላቸው የአስፈፃሚ አካላት መሥሪያ ቤቶች አንድ የድጋፍ ሰጪ ማዕከል በጋራ ሊጠቀሙ ይችላሉ፤
6. በየደረጃው ያሉ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች በየአስተዳደር እርከኑ እንደ አስፈላኒነቱ ተቀናጅተው ወይም ተጣምረው ሊደራጁ ይችላሉ፤

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 34

### አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ስለማደራጀት

የመስተዳድር ምክርቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት፣ ማንኛውም አስፈጻሚ አካል እንዲታጠፍ ወይም ከሌላ አስፈጻሚ አካል ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፋፈል ወይም ተጠሪነቱ ወይም ሥልጣንና ተግባሩ እንዲለወጥ ወይም አዲስ አስፈጻሚ አካል እንዲቋቋም

በማድረግ የክልሉን መንግሥት አስፈጻሚ አካላት መስሪያ ቤቶችን የማደራጀት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## አንቀጽ 35

## የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸዉ ሕጎች

1. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 190/2015 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
2. የክልሉ የመንግስት የጋራ ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣዉ ደንብ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤
3. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## አንቀጽ 36

## መብትና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

1. ለመንግስት የጋራ ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጽህፈት ቤት ተሰጥቶ የነበረው የግዥ ተግባር እና ሀላፊነት ለየክልሉ ተቋማቶች የተላለፈ ሲሆን የገበያ ጥናትና የንብረት ማስወገድ ተግባርና ሀላፊነቶች ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በዚህ አዋጅ ተላልፈዋል፤

## አንቀጽ 37

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በመስተዳድር ምክር ቤት የወጡ ደንቦች እና በክልሉ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 190/2015 ዓ.ም መሰረት የወጡ ሥልጣንና ተግባር ለማስፈፀም አግባብነት ያላቸው ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች በሌሎች ደንቦች፣መመሪያዎች ወይም ማኑዋሎች እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤
2. በዚህ አዋጅ መሰረት ከአንደኛዉ ተቋም ወደ ሌላኛዉ ተቋም ተግባርና ኃላፊነቱ የተጠቃለለዉ የመንግስት ተቋም በዘርፉ የሚሰሩ ሠራተኞች በተጠቃለለዉ ተቋም ዉስጥ ሠራተኞች ሆነው ይቀጥላሉ፡፡

3. የሚከፋፈሉ እንዲሁም የሚታጠፉ ተቋማትን ቁሳዊ እና ፋይናንሻል ሀብት በተመለከተ እንደ ክልል ከሚመለከታቸው መሰሪያ ቤት በሚዋቀር ኮሚቴ መሰረት ስራው ተሰርቶ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ውሳኔ ሲያገኝ የሚተላለፍ ይሆናል፣

## አንቀጽ 38

## ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንቦችን መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፤
2. ይህን አዋጅና አዋጁን ተከትለዉ የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎችን የመስተዳድር ምክር ቤት አባል የሆኑ የአስፈፃሚ አካላት መስሪያ ቤቶች ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

## 3. አንቀጽ 39

## አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሐምሌ 18 ቀን 2015 /ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ ሐምሌ18/2015 ዓ.ም

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት